# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድህረ-ምረቃ መርሀ-ግብር

# አማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድ በወንድና ሴት ተማሪዎች መካከል ያለ ንጽጽር በጮሌ ሁለተኛደረጃ ት/ቤት በ9ኛ ክፍል አማርኛ አፊፊት ተማሪዎች የቋንቋ ክሂል ችሎታ ላይያተኮረ

ለተግባራዊ ስነ-ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ ዲግሪ

በከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ


ልዩወርቅ እምሻው አምዴ


ሐምሌ2015 ዓ/ም

አዲስ አበባ

# አማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድ በወንድና ሴት ተማሪዎች መካከል ያለ ንጽጽር  በጮሌ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በ9ኛ ክፍል አማርኛ አፈፊት ተማሪዎች የቋንቋ ክሂል ችሎታ ላይ ያተኮረ


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮሚዩኒኬሽን  ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት


የድህረ-ምረቃ መርሃ-ግብር

ለተግባራዊ ስነ-ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤመ.ኤ ዲግሪ በከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት


በ

ልዩወርቅ እምሻው አምዴ

የጥናቱ አማካሪ

ዶ/ር ግርማ ገብ


ሐምሌ 2015 ዓ/ም

አዲስ አበ

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የስነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዘጠኝነትና ተግባቦት ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ፣ ስንስጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት**

**የድህረ- ምረቃ መርሃ- ግብር**

**የፈተና ቦርድ ማረጋገጫ**

**ይህ ጥናት "አማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድ በወንድና ሴት ተማርዎች መካከል ያለ ንጽጽር በጮሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል አማርኛ አፈፊት ተማርዎች የቋንቋ ክሂል ችሎታ ላይ ያተኮረ" በሚል በተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ለማስተማር የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ሲሆን፣ መስፈርት ለሟሟላቱም በጥናቱ አማካሪና ገምጋሚዎች ተረጋግጧል፡፡**

**የፈተና ቦርድ አባላት**

**አማካሪ**

**ስም--------------------------ፊርማ-------------------ቀን----------------------**

**የውስጥ ፈታኝ**

**ስም-------------------------ፊርማ--------------------ቀን----------------------**

**የውጭ ፈታኝ**

**ስም----------------------ፊርማ----------------------ቀን-----------------------**

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

ማውጫ ........ ii
የሠንጠረዥ ማውጫ ........ v
ምስጋና ........ vi
አህጽሮተ ጥናት ........ vii
ምዕራፍ አንድ ........ 1
1.መግቢያ ........ 1
1.1.የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 3
1.3 የጥናቱ አላማ ........ 5
1.3.1. አጠቃላይ ዓላማ ........ 5
1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች ........ 5
1.4.የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ........ 6
1.5.የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 6
1.6.የጥናቱ ውስንነት ........ 6
ምዕራፍ ሁለት ........ 8
ክለሳ ድርሳናት ........ 8
2.1 የጾታ ምንነት ........ 8
2.2.1 የጾታ ልዩነትና የቋንቋ ትምህርት ........ 10
2.4. ሴትና ወንድ ተማሪዎች በትምህርት ረገድ ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት ........ 12
2.5. የተቀናጁ ሙከራዎች (Integrative Tests) ........ 14
2.5.1. የግንዛቤ መለያ ሙከራ ........ 15
2.5.1.1. የግንዛቤ ሙከራዎች ጠንካራና ደካማ ጎኖች ........ 16

2.5.2.የቃል ጽህፈት ሙከራ ........ 16

2.5.የቃል ፅህፈትና የክሂል ዘርፎች ትስስር ........ 18

2.6..ፎግኢንዴክስ ........ 19

2.7.የቀደምት ሀገርኛ ጥናቶች ቅኝት ........ 22

ምዕራፍ ሶስት ........ 23

3.የጥናቱ ዘዴና አካሄድ ........ 23

3.1. የተጠኚዎች አመራረጥ ........ 23

3.1.1. የትምህርት ቤት አመራረጥ ........ 23

3.1.2. የተማሪዎች አመራረጥ ........ 23

3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 24

3.2.1. የግንዛቤ ሙከራ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ........ 24

3.2.2. የቃል ጽህፈት ........ 27

ምዕራፍ አራት ........ 29

4.የመረጃ አቀራረብና ትንተና ........ 29

4.1. የጥናቱ መረጃ ትንተና ........ 29

4.2. የውጤት ማብራሪያ ከጥናቱ ዓላማና መሰረታዊ ጥያቄዎች አንጻር ........ 36

ምዕራፍ አምስት ........ 39

5. ማጠቃለያና አስተያየት ........ 39

5.1 ማጠቃለያ ........ 39

ዋቢ ጽሁፎች (Bibliography) ........ 43

አባሪ ሀ-1 ........ 49

አባሪ ሀ- 2 ........ 50

አባሪ ሀ- 3 ........ 52

አባሪ ሀ-4 ........ 54

አባሪ ሀ-5 ........ 55

አባሪ ለ-1 ..... 56
አባሪ ለ-2 ..... 57
አባሪ ሐ-1 ..... 58
አባሪ ሐ-2 ..... 59
አባሪ መ-1 ..... 60
አባሪ መ-2 ..... 61
አባሪ መ-3 ..... 63
የሴት ተማሪዎች የግንዛቤ መለያ ሙከራ ውጤት ..... 63
አባሪ መ-4 ..... 65
የሴት ተማሪዎች የቃል ጽህፈት ሙከራ ውጤት ..... 65
አባሪ - ሠ 1 ..... 67
አባሪ - ሠ 2 ..... 67
አባሪ - ረ ..... 68
አባሪ - ሰ ..... 68

## የሠንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ 1፡- ገኒንግ ፎግ ኢንዴክስ (Fog Index)…………………………………………...….20
ሠንጠረዥ 2፦ በግንዛቤ መለያ ሙከራ ወንድ ተጠኚ ተማሪዎች ያስመዘገቡት ውጤት……………33
ሠንጠረዥ 3፡- በቃል ጽህፈት ሙከራ ወንድ ተጠኚ ተማሪዎች ያስመዘገቡት ውጤት…………………………………………………………………………………33
ሠንጠረዥ 4፡- በግንዛቤ መለያና በቃል ጽህፈት ሙከራ ወንድ ተጠኚ ተማሪዎች ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት (M) እና ስታንዳርድ ዲቪየሽን (Sd) ንጽጽርና በሁለቱ መካከል ያለው ተዛምዶ……………………………………………………………...………. 34
ሠንጠረዥ 5፡- በግንዛቤ መለያ ሙከራ ሴት ተጠኚ ተማሪዎች ያስመዘገቡት ውጤት…….....………35
ሠንጠረዥ 6፡- በቃል ጽህፈት ሙከራ ሴት ተጠኚ ተማሪዎች ያስመዘገቡት ውጤት………………35
ሠንጠረዥ 7፡-በግንዛቤ መለያና በቃል ጽህፈት ሙከራ ወንድ ተጠኚ ተማሪዎች ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት (M) እና ስታንዳርድ ዲቪየሽን (Sd) ንጽጽርና በሁለቱ መካከል ያለው ተዛምዶ……....36
ሠንጠረዥ 8፡- አጠቃላይ ወንድና ሴት ተማሪዎች በግንዛቤ መለያ ሙከራ ያገኙት ውጤት ንጽጽር36
ሠንጠረዥ 9፡-አጠቃላይ ወንድና ሴት ተማሪዎች በቃል ጽህፈት ሙከራ ያገኙት ውጤትንጽጽር…..37
ሠንጠረዥ 10:-በሁለቱ ሙከራዎች በሁለቱም ጾታዎች የተገኘው ውጤት ንጽጽር ……………….38

# ምስጋና

የድህረ ምረቃ ትምህርቴን ጀምሬ እስካጠናቅቅ ድረስ ካስተማሩኝ መምህሮቼ ጀምሮ የተለያየ ድርሻ ያላቸውን በርካታ ሰዎች ላመሰግን እወዳለሁ። በተለይ ግን እውቅና ሰጥቼ የላቀ ምስጋና የማቀርበው በቅድሚያ በነገር ሁሉ የረዳኝን የድንግል ማርያም ልጅ ልዑል እግዚአብሔርን ነው። በመቀጠል በተጣበበ ጊዜ ስራዎቼን እያዩ በርቺ ቀጥዪ በማለት አስተያየት በመስጠት እዚህ እንድደርስ የረዱኝን አማካሪዬን ዶ/ር ግርማ ገብሬ ከልብ አመሰግናለሁ።

ሌላው ሳላመሰግናቸው ብቀር ውስጤ በቅሬታ ሊሞላ እና ውለታቢስ ሊያደርገኝ ስለሚችል ያላቸውን ሳይነፍጉ የሰጡኝ ውድ እና ክቡር መምህሮቼን ከልብ ላመሰግናቸው እወዳለሁ።

በመቀጠል በመደበኛ ስራዬ፤ በአሳለፍኳቸው ተከታታይ የክረምት ትምህርት ዓመታት ውስጥ እና ይህየጥናት ስራ ከመነሻው ጀምሮ ፍጻሜ እስኪደርስ ከጎኔ ሳይለዩኝ፤ ለስራዬ መሳካት ምንም ሳይሰስቱ፣ ፍቅርና እንክብካቤ ለቸሩኝ የገንዘብ እና የማቴሪያል ድጋፍ ላደረጉልኝ ባለቤቴና ልጆቼ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

በመጨረሻም ከትልመ ጥናቱ ጀምሮ እስከ ዋናው ጥናት መጠናቀቅ ድረስ ፈተናዎችን በማረም፣ አስተያየቶችን በመስጠት ሙያዊ እገዛቸው ያልተለየኝ የጮሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፤ እና በጥናቱ የተሳተፉትንና ጠቃሚ መረጃ የሰጡኝን የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን ከልብ አመሰግናለሁ።

# አህጽሮተ ጥናት

*የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ተቀዳሚ አላማ አማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድ በወንድና ሴት ተማሪዎች መካከል ያለ ንጽጽር በጮሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ክሂል ችሎታ ምን እንደሚመስል መመርመር ነው።ይህም ማለት በወንድና ሴት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ ክሂል ችሎታ ተጨባጭ የሆነ ልዩነት መኖር አለመኖሩን መመርመርና ልዩነትም ካለ በሁለቱ ጾታዎች መካከል በምን ያህል ስፋት ይገኛል የሚለውን ለመለየት ነው። ይህ ጥናት በጾታዎቹ መካከል ያለውን አጠቃላይ የቋንቋ ክሂል ችሎታ ልዩነት ለመለካትየተጠቀመው የግንዛቤ መለያና የቃል ጽህፈት ሙከራዎችን ነው። ለጥናቱ በመረጃ ምንጭነት ያገለገሉት በጮሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። በ2015 ዓ.ም. በትምህርት ገበታ ላይ ከነበሩት አጠቃላይ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል 91 ወንድና 105 ሴት ተማሪዎች በተጠኚነት ተመርጠዋል።ለግንዛቤና ለቃል ጽህፈት ሙከራዎች ያገለግላሉ ተብለው የተመረጡት አራት ምንባቦች (ሁለት ለግንዛቤ መለያና ሁለት ለቃል ጽህፈት ሙከራ) በስራ ላይ ከመዋላቸው በፊት የጥናቱ ትኩረት ለሆኑት በዘጠነኛ ክፍል ደረጃ ለሚማሩ ተማሪዎች መመጠን አለመመጠናቸውን ለማረጋገጥ በተነባቢነት ቀመር (ፎግ ኢንዴክስ) መሰረት ተሰልተው የሚመጥኑ መሆናቸው ታውቋል። በዚህም መሰረት በወንድና ሴት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በአጠቃላይ የቋንቋ ክሂል ችሎታ አንጻር ከግንዛቤ የሚገባ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ተጠኚ ተማሪዎቹ በሁለቱ ሙከራዎች ያስመዘገቡት አማካይ ውጤትና ስታንዳርድ ዲቪዬሽን ከተተነተነ በኋላ የአጠቃላይ ውጤቱ በቲቴስት ቀመር መሰረት ተሰልቶ በግንዛቤ መለያና በቃል ጽህፈት የተመዘገበው ነጥብ በቅደም ተከተል 0.8509 እና 1.8505 ሲሆን ይህ ውጤት ደግሞ ልዩነት መኖሩን ለማረጋገጥ ከሚጠበቀው ዋጋ 1.9723 በታች ነው። በዚህም ማረጋገጥ የተቻለው በሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ አጠቃላይ ክሂል ችሎታ ከግንዛቤ የሚገባ ልዩነትአለመስተዋሉን ነው።*

# ምዕራፍ አንድ

## 1.መግቢያ

### 1.1.የጥናቱ ዳራ

ትምህርት የጾታ እኩልነትን ጨምሮ ማህበራዊ እኩልነት ለማስፈን ሁነኛ የሆነ መሳሪያ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ የትምህርት ተደራሽነት እኩልነትን ማረጋገጥ ቅድሚያ የሚሰጠው ማህበራዊ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮአዊና ግልጽ መሆን ያለበት ነገር ነው፡፡

የትምህርት አቀባበል ዘዴና ስልት ለብዙ ጊዜያት ቆይቶ እስካሁን የዘለቀ ለብዙዎች የመነጋገሪያና የመወያያ ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡ብዛት ያላቸው አጥኚዎች የትምህርት አቀባበል ዘዴና ስልትን የሚያውኩ ምክንያቶችን ለማረጋገጥ ጥናት እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ከነኚህም ምክንያቶች ውስጥ የጥናታቸውን ትኩረት የሳበው በጾታ መካከል ያለው የትምህርት አቀባበል ልዩነት ነው፡፡

በቁጥር አናሳ የማይባሉ አጥኚዎች በጥናቶቻቸው ለማሳየት እንደሞከሩት ምንም እንኳን ሴት ተማሪዎች ከወንድ አቻዎቻቸው ያነሰ ተፈጥሮአዊ ችሎታ ባይኖራቸውም እንደ አጠቃላይ በመማር ማስተማር የክፍል ውስጥ ክንውንና በሚያደርጉት ተሳትፎ እንዲሁም አብላጫ ባላቸው የትምህርት ዓይነቶች የሚያስመዘግቡት ውጤት በአንጻራዊ መልኩ ከወንድ ተማሪዎች ያነሰ እንደሆነ አደም ገብሬ (1990)፡ ስዩም ተፈራ (1991)፡ እንዲሁም ገነት ዘውዴ (1991) ባካሄዷቸው ጥናቶች በሀገራችን በተለያዩ የትምህርት እርከኖች ላይ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ባሉ ሴት ተማሪዎች በጾታቸው ሳቢያ በሚያጋጥሟቸው ችግሮች የተነሳ የሚየገኙት ውጤት ከወንድ ተማሪዎች ያነሰ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

Ebel (1999) እንደገለጸው ከሆነ ወንዶችና ሴቶች የተለያየ የትምህርት አቀባበል ዘዴና ስልት አላቸው፡፡Ebel (1999) በጥናቱ በዝርዝር እንዳስቀመጠው ከሆነ ወንዶች ከሴቶች በበለጠ ከማዳመጥ ይልቅ በማየት የተሻለ መማር እንደሚችሉ ነው፡፡በሌላ በኩል ደግሞ ሴቶች በመናገርና በማዳመጥ የትምህርት አቀባበል ዘዴና ስልት ከወንዶች የተሻሉ መሆናቸውን ገልጿል፡፡

Tannen (1992) በጥናቱ የጠቆመው ማጠቃለያ የEbel (1999)ን የጥናት ውጤት የሚያጠናክር ነው፡፡ እንደ Tannen (1992)ጥናት ከሆነ ወንድ ተማሪዎች በቡድን ውስጥ ያላቸውን ቦታ ለማሳየት ህዝብ በተሰበሰበበት አውድ መናገር የሚመርጡ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሴት

ተማሪዎች ንግግር የእርስበርስ ግንኙነትን የሚያጠናክር መንገድ ነው ብለው ስለሚያስቡ በግል ጉዳዮች አውድ ላይ መናገርን ይመርጣሉ፡፡

Global Partnership for Education (2021) አተያይ ከሆነ በትምህርት ላይ ያለው የጾታ ልዩነት ሴት ተማሪዎች መሰረታዊ የሆነውን ትምህርት የማግኘት የሰው ልጆች መብት እንዳይጠቀሙ ያግዳቸዋል፡፡

ሁሉን አቀፍ በሆነ አለም አቀፍ የሴቶች እንቅስቃሴ የተነሳ ላለፉት አራት አምስት አስርት አመታት የጾታ ጉዳይ አንዱ ከቋንቋ ጋር ተያያዥነት ያለው ጉዳይ መሆን ችሏል፡፡ በዚህም የተነሳ በትምህርት መስክ የጾታ ልዩነትን መነሻ ያደረጉ በርከት ያሉ የጥናትና ምርምር ስራዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተደረጉ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የጾታ ልዩነት ያለውን ሚና ለማሳየት እየተሞከረ ይገኛል፡፡

በጾታና ቋንቋን በመማር መካከል ያለውን ተዛምዶ ለማወቅ በርከት ያሉ አለም አቀፍ ጥናትና ምርምሮች ተሰርተዋልም እየተሰሩም ይገኛል፡፡ Oxford, R. (1990) እንደገለጸው ከሆነ ጾታ ቋንቋን በመማር ሂደት ረገድ ተጨባጭ ተጽዕኖ እንደሚኖረው ገልጿል፡፡ እንደ ኦክስፎርድ አገላለጽ ከሆነ ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች የተለያዩና ብዛት ያላቸው የቋንቋ መማሪያ ስልቶችን እንደሚጠቀሙ ያሳያል፡፡

Xiufang Xia (2013), የጾታ ልዩነት ከቋንቋ አጠቃቀም አኳያ በሚል ርዕስ ባደረገት ጥናት በአነጋገር ስልት፤ በቃላት ዜማ አሰባበር፤ በቃላት አጠቃቀም፤ በአረፍተ ነገር ምስረታና በመሳሰሉት ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በወንድና ሴት መካከል ያለውን ልዩነት ለመመልከት ሞክረዋል፡፡ የጥናታቸውም ውጤት በወንድና ሴት መካከል የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነቶች እንዳሉ ያረጋግጣል፡፡

በሀገራችን በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ አጥኚዎች የተጠኑ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከሆነ በተለያዩ የትምህርት እርከኖች ላይ የሚገኙ ሴት ተማሪዎች ከጾታቸው ጋር ተያይዞ በሚደርስባቸው ጫና የተነሳ የትምህርት ውጤታቸው በአንጻራዊ መልኩ ከወንድ አቻዎቻቸው ያነሰ ነው፡፡ (Adem and Gebre 1990፡ seyoum (1991) ፡፡

እንደ Tsege (1991)፤ Haregewion and yusuf 1994) ጥናት ከሆነ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተናዎች በሚያስመዘግቡት ዝቅተኛ ውጤት የተነሳ ወደተለያዩ የከፍተኛ ትምህርት

ተቋማት የሚገቡት ሴት ተማሪዎች ቁጥር እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡ አጥኚዎቹ በጥናታቸው ለማሳየት እንደሞከሩት በኢትዮጵያ ውስጥ ትምህርታቸውን ይከታተሉ ከነበሩት ጠቅላላ ተማሪዎች መካከል የሴት ተማሪዎች ቁጥር 11 በመቶ ብቻ ነው፡፡ አጥኚዎቹ አክለውም ከጾታ ጋር በተያያዙ በርካታ ችግሮችና ማህበራዊ እንቅፋቶች ሳቢያ የትምህርት ዕድሉ ካጋጠማቸው ሴቶች መካከል አብዛኞቹ ትምህርታቸውን በአግባቡ መከታተል እንደሚያዳግታቸው ይገልጻሉ፡፡

እንደ እነ Betz, and Fitzegerald. (1987)፤ Imani Swilla (1993)፤ እንዲሁም ገነት ዘውዴ (1991) ጥናት ግኝት ከሆነ ከአጸደ ህጻናት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ባሉት የትምህርት እርከኖች የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ መምህራን ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጡት ከሴቶች ይልቅ ለወንድ ተማሪዎቻቸው ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው በትምህርት አቀባበል ዙሪያ መምህራን ለሴት ተማሪዎቻቸው ያላቸው አመለካከት አናሳ መሆኑን ነው፡፡

ከፍ ብሎ ለመጠቆም እንደተሞከረው በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ አጥኚዎች የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች ያነሰ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ እንዳላቸው ነው፡፡ ባጠቃላይ በአጥኚዎቹ የተካሄዱት ጥናቶች ከሚያመላክቱት ሃሳቦች አጥኚዋ ለመረዳት የቻለችው በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለው ልዩነት በተፈጥሮ የጾታ ልዩነት ሳይሆን ካለው ከማህበረሰቡ አመለካከት ወይም ኋላ ቀር አስተሳሰቦች ማለትም ሴትን ልጅ ወደ ትምህርት ቤት ከመላክ ይልቅ መማርና ማወቅ ያለባት የቤት ውስጥ ባልትናን ነው ከሚሉ ኋላ ቀር አስተሳሰቦች የተነሳ ትምህርት የሚያስፈልገው ለወንዶች እንደሆነ የሚያስቡ በመኖራቸው እና ከዚህም የተነሳ አዋቂ ናቸው የሚባሉ መምህራኖች እንኳ ያላቸው አመለካከት ወንዶች ተማሪዎችን የሚያበረታቱ ሴት ተማሪዎችን ግን ዝቅ አድርገው ለማየት የሚፈልጉ መምህራን እንዳሉም የሚያሳይ ነው፡፡

## 1.2.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የሴቶች በራስ መተማመን ይበልጥ የሚወሰነው ከሌሎችጋር በማነፃፀር ነው፡፡አራጋው(2003) ፊልድማን (1996)ን ጠቅሶ እንዳብራራው አስቸጋሪ ተግባራትን በውጤታማነት በመፈፀም ረገድ በአጠቃላይ የወንዶች በራስ መተማመን ከሴቶች የበለጠ ነው፡፡አራጋው ጨምሮ እንዳብራራው ወንዶችና ሴቶች ስለራሳቸው ችሎታ ያላቸው አዎንታዊ አስተሳሰብ የተለያየ ነው በማለት ሲገልጹ ከዚህም በተጨማሪ ወደፊት ለሚከናወኑ ተግባራት ለራሳቸው ስኬት ባላቸው ግምት ወንዶችና ሴቶች የተለያዩ ናቸው፡፡

በሁለተኛ ደረጃና በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት እርከኖች ሴቶች ከወንዶች ዝቅያለ በራስ መተማመን አላቸው በማለት አራጋው(2003) Bori and Tombori (1995); Bank(1999) ጠቅሶ ያብራራል። አራጋው ይበልጥ ሲያብራራው ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ያለው ማህበራዊ ግንኙነታቸው በጣም ዝቅተኛ ነው።በርግጥ አልፎ አልፎ ዝቅተኛ ቁጥር ያላቸው ሴት ተማሪዎች ሽልማት ያገኛሉ።ውስብስብና ረቂቅ ጥያቄዎችን ዝቅተኛ ግልፅነት ያላቸው የትዕዛዝማስተላለፊያ መመሪያዎችን ለመመለስና ለመቀበል ፍላጎት የላቸውም።ክሂሎችን እስኪካኗቸው ድረስ ልምምድ ለማድረግ ጠንካሮች ናቸው።ከወንዶች ጋር ሲነፃፀሩሴቶች በክፍል ውስጥ ጥቂት ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ ዝቅተኛ ግብረ-መልስም ያገኛሉ።ይህ ልዩነት በሴቶች በኩል ዝቅተኛ በራስ መተማመን እንዳለ እንዲገመት ያደርጋል።

ከዚህ ቀደምም ሆነ አሁንም በፆታና ትምህርት መካከል ስላለው ግንኙነት ጥናቶች ተደርገዋል እየተደረጉም ይገኛሉ። አራጋው አርያና (2010)ን በመጥቀስ እንደሚገልፀው ትምህርት ከፆታ አንፃር የተለያየ ብያኔ እንደሚሰጠው የትምህርት ውጤትም ከፆታ አንፃር ልዩነት አለው ወደሚል ድምዳሜ እንደደረሰ በጥናቱ ላይ አብራርቷል። Aryana, Jackob(2002)ን ዋቢ በማድረግም በዩኒቨርሲቲና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሴቶች ከወንዶች የተሻለ ይሰራሉ፤ ከፍተኛ ውጤትም ያመጣሉ በማለት ይገልፃሉ። በአንፃሩ ደግሞ ፆታን እና የትምህርት ውጤትን የተለያዩ ነገሮች ናቸው በማለት የሚያጠቃልሉ መኖራቸውንም ጨምረው አስፍረዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ከዚህ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን በሀገራችን የተካሄዱ ጥናቶችን ለመፈተሽ አጥኚዋ ጥረት አድርጋለች።

በሀገራችን በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ አጥኚዎችና በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች በሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል ያለውን ልዩነት የሚያሳዩ ጥናቶች የተሰሩ ቢሆንም አብዛኞቹ የተሰሩት በየትምህርት ዓይነቱ በጥቅሉ ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች ያነሰ ተሳትፎና ውጤት እንዳላቸው የሚያመላክቱ ናቸው። የዚህ ጥናት አቅራቢ ማረጋገጥ እስከቻለችው ድረስ ግን ከቋንቋ ጋር ተያይዞ በተናጠል በሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል የተሰሩ በዛ ያሉ ጥናቶች የሉም።

ይሁን እንጂ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ አጥኚዋ ይህንን ጥናት ለማድረግ ስትነሳሳ የጾታ ልዩነት አማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድ ያለው ሚና በእንጦጦ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች አጠቃላይ የቋንቋ ብቃትን የሚዳስስ ጥናት ቀደም ብሎ በፋንቱ ደምሴ መደረጉን መረዳት ችላለች።

ይህን ጥናት ከፋንቱ ደምሴ ጥናት የሚለየው የተሰራበት ጊዜ ጥናቱ የተደረገበት ቦታና የክፍል ደረጃ ሲሆኑ በተለይ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክልን አጠናቀው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚጀምሩበት የትምህርት እርከን በመሆኑ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በቋንቋ ዙሪያ በሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል የሚስተዋለውን ልዩነት ለማሳየት ተገቢ የክፍል ደረጃና መልካም አጋጣሚ ይሆናል ብላ አጥኚዋ ታምናለች፡፡

አጥኚዋ በኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን ጮሌ ወረዳ በጮሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ ለረጅም አመታት ያህል ስታስተምር በሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የክፍል ተሳትፎ ላይ የተወሰነ ልዩነት እንዳለ ለማስተዋል ችላለች፡፡ ስለሆነም በዘጠነኛ ክፍል ወንድና ሴት ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ ክሂል ዙሪያ የሚስተዋል ተጨባጭ ልዩነት አለ ወይ? ልዩነቱ ካለስ በምን ደረጃ ላይ ይገኝ ይሆን? የሚል ጉልህ ጥያቄዎች በአዕምሮዋ በመጫሩ በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ጥልቅ የሆነ ጥናትና ምርምር እንድታደርግ ከፍተኛ ፍላጎት አደረባት፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አጥኚዋ በልምድ ከተገነዘበችው ሴት ተማሪዎች ከወንዶች አቻዎቻቸው አንጻር ውጤታቸው የተሻለ እንዲሆንና እንዲበቁ በሚል እሳቤ በየትምህርት ቤቱ የተለየ ድጋፍ፣ ቲቶርና ተጨማሪ እገዛ ይሰጣቸዋልከሚለው በመነሳት ማንኛው ወገን በቋንቋ ክሂል ዙሪያ የተሻለ ሚዛን ይደፋል የሚለውን በጥልቀት ለማየት በዚህ ጥናት ለመፈተሽ ተነሳሳች፡፡

## 1.3 የጥናቱ አላማ

### 1.3.1. አጠቃላይ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ አማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድ በወንድና ሴት ተማሪዎች መካከል ያለ ንጽጽር  በጮሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ አፊ-ፊት ተማሪዎች የቋንቋ ክሂል ችሎታ ምን እንደሚመስል መመርመር ነው፡፡

### 1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች

ከዚህ ዋና አላማ በተጨማሪ ይህ ጥናት የሚከተሉትን ዝርዝር አላማዎች አካቷል፡፡

- በሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክሂል ብቃት ችሎታ ተጨባጭ ልዩነት መኖር አለመኖሩን መለየት፡፡
- የጾታ ልዩነት የአማርኛ ቋንቋ ክሂልን ከመማር አንጻር ያለውን አንድምታ መፈተሽ ነው፡፡

## 1.4.የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች

ይህ ጥናት ከላይ የተጠቀሱትን ዓላማዎችን መነሻ አድርጎ ተጠኝዎችን መርጦ፣ መረጃ ሰብስቦ ከተነተነ በኂላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል።

1. በዘጠነኛ ክፍል ሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክሂል ብቃት ችሎታ ተጨባጭ ልዩነት አለ ወይስ የለም?
2. የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ክሂልን ከመማር አንጻር የጾታ ልዩነት ያለው አንድምታ ምንድነው?

## 1.5.የጥናቱ ጠቀሜታ

ከላይ ከተጠቀሱት ዓላማዎች በመነሳት ይህ ጥናት ለአማርኛ ቋንቋመምህራን፣ ለትምህርት ባለሙያዎች እንዲሁም ለተማሪዎች የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል።

- ሴትና ወንድ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክሂል ችሎታ ላይ ልዩነት እንዳላቸውና እንደሌላቸው በመለየት የትምህርት አሰጣጡን በክፍተታቸው ረገድ ማስተካከያ ለማድረግ ያስችላል።
- የሴትና ወንድ ተማሪዎች ልዩነት በአማርኛ ቋንቋ ክሂል ዘርፎች በየትኞቹ ላይ እንደሚበረታ በመለየትና ችግሩን ለመፍታት በአማርኛ ቋንቋ መምህራን መወሰድ ያለበትን እርምጃ ለመጠቆም ያስችላል።
- ለአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ለትምህርት ባለሙያዎች የመፍትሄ ሀሳብ ይጠቁማል።
- ይህ ጥናት ባተኮረበት ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ለሚከናወኑ ቀጣይና ተዛማጅ ጥናቶች መነሻ ይሆናል።

## 1.6.የጥናቱ ውስንነት

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት አርሲ ዞን ጮሌ ወረዳ በጮሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም. በዘጠነኛ ክፍል በመማር ላይ ባሉ ተማሪዎች ላይ ነው።በጥናቱ የተካተቱት ሴትና ወንድ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ ዋና ዓላማ አድርጎ የተነሳውም በወንድና ሴት ተማሪዎች መካከል የአማርኛ ቋንቋ ክሂል ችሎታ ተጨባጭ የሆነ ልዩነት መኖር አለመኖሩን መለየት ነው።

አጥኚዋ በዘጠኛ ክፍል ቢቻ የተወሰንነችበት ምክንያት የምታስተምረው በዚህ ክፍል በመሆኑና ይህን ርእስ ለመምረጥ የቻለችውም በምታስተምርበት ጊዜ በዚሁ ክፍል ካስተዋለቻቸው ችግሮች በመነሳት ስለሆነ ነው፡፡ እንዲሁም ካለው የጊዜ፣ የባጀት እጥረት አንጻር በዚህ ክፍል ላይ ብቻ ለመወሰን ተገዳለች፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 የጾታ ምንነት

**ስለ ጾታ በተለያዩ ምሁራን በተለያዩ ጊዜያት የተሰጡት ብያኔዎች ጭብጣቸው ተመሳሳይ ቢሆንም የተገለጹበት መንገድ ግን የተለያየ ነው። ከነዚህም ውስጥ የተወሰኑትን እንመልከት።**

እንደ Olsen, (2000)፣Subbo (2002), Hirut (2002) አገላለጽ ተፈጥሮ የግለሰቦችን ፆታ ሲወስን፤ ባህል ደግሞ ለሴት ወይም ለወንድ ፆታ የሚኖረውን አመለካከትና ባህሪ ያንፀባርቃል። በእያንዳንዱ ባህል ውስጥ ግለሰቦች ለሁለቱም ፆታዎች የሚሰጡት ግምት ይኖራል። ይህ የስርዓተ ፆታ ግምት ለሴት ወይም ለወንድ ፆታ የሚሰጡ ባህርያትን እና አመለካከቶችን ይጠቁማል።

Datnow, A. and Hubberd, L (2002)፤ Suzanne, W. (2002) , Anker (1993) በበኩላቸው ሲያብራሩ ፆታ በሰው ልጅ የህይወት ዘመን ቋሚ የሆነ ስነ-ፍጥረታዊ ባህሪ ነው ይላሉ። በዚህም በሴት እና በወንድ መካከል እንደሀብለብራሔ (ሆርሞን) እና መራቢያ አካላት ያሉት ስነ-ፍጥረታዊ ልዩነቶች በሁሉም የአለም ክፍሎች ተመሳሳይና ከጊዜ ወደ ጊዜ ለውጥ የሌላቸው ናቸው።

ከላይ የቀረበውን ሀሳብ በማጠናከር እነ Lindsey, L.L.. (2005)፤ Santrock, J.W. (2001) Papolia, D.E. and et al. (1999) and Anderson, M.L. (1988) እንዳስገነዘቡት ፆታ የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአንድን ሰው ዝርያ እና አካላዊ የሆነውን መለያ ነው። ይህ እውነት ስነ-ፍጥረታዊ ሲሆን የስርዓተ-ፆታ መገለጫ ግን ሊሆን አይችልም። በዚህም አንድ ሰው ሴት ወይም ወንድ ሆኖ ተወለደ ማለት እሷ ወይም እሱ ሴትነት ወይም ወንድነቱ ላይ ተፈጥሮ አድሎ አድርጋለች ማለት አይደለም ሲሉ ይገልፃሉ።

## 2.2 የጾታ ልዩነትና ትምህርት

በትምህርት መስክ የጾታ ልዩነትን መነሻ ያደረጉ በርከት ያሉ የጥናትና ምርምር ስራዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተደረጉ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የጾታ ልዩነት ያለውን ሚና ለማሳየት እየተሞከረ ይገኛል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ በሀገር ውስጥ የተከናወኑ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት፤ ምንም እንኳን በትምህርት ገበታ ላይ የሚገኙ ኢትዮጵያውያት ተማሪዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የሄደ ቢሆንም፤ ከወንዶች ቁጥር ጋር በሚነፃፀርበት ጊዜ ግን የሴቶች ቁጥር እጅግ ዝቅተኛ

ከመሆኑም በላይ በአጠቃላይ ትምህርታዊ ተሳትፏቸውም ሆነ በየትምህርት ዓይነቱ በሚያስመዘግቡት ውጤት ረገድም ከሴቶች ይልቅ ወንዶች ተማሪዎች የተሻሉ ሆነው መገኘታቸው ተረጋግጧል (Tsege 1991፣ Seyoum 1991)፡፡

Adem and Gebre (1990), Seyoum (1991), Tsege (1991), Genet (1991) በዚህ ርዕስ ዙሪያ ያጠኗቸው ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከዝቅተኛ ክፍሎች ጀምሮ በየደረጃው በሚገኙ የትምህርት ተቋማት ከሚማሩ ተማሪዎች መካከል በየክፍል ደረጃው ከሚደግሙትና ከነጭራሹትምህርታቸውን ለማቋረጥ ከሚገደዱት ውስጥ የሴቶች ቁጥር ከወንዶች ቁጥር በእጅጉ ያመዝናል፡፡

የፆታ ልዩነትና ትምህርትን በተመለከተ  የተከናወኑት የምርምር ስራዎች በተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች በሚያስመዘግቡት ውጤትና ለየትምህርት አይነቱ በሚኖራቸው አመለካከትና ዝንባሌ ረገድ በወንድና ሴት ተማሪዎች መካከል ልዩነት አለ የለም በሚለው ጉዳይ ላይ የተለያዩ ሃሳቦችን ይሰነዝራሉ፡፡

በርካታዎቹ ይህን መሰል የጥናት ግኝቶች፤ (Hilton, Thomas and G.berglund.1974፣ Makoby. E.E and Jackline C.N 1974፣ BETZ, and Fitzegerald 1987፣ Benbow, C. and J.C. Stanely,1985፣ Johnes, and Smart.1995)፡፡ ከትምህርት ጋር በተያያዘ ተግባራት አኳያ ከፆታ ልዩነት የሚመነጩ ልዩነቶች መኖራቸውን ሲያረጋግጡ በአንፃሩ በተለያዩ አዕምሯዊ ተግባራት ረገድ በወንዶችና በሴቶች መካከል የሚታየው ልዩነት ከግምት የማይገባ መሆኑን Marsh (1989) and Warrik and Naglieri  (1993) የሀይዲን የጥናት ግኝት በመጥቀስ ይጠቁማሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ ረገድ ምንም ልዩነት አለመታየቱን የሚያረጋግጡ የጥናት ግኝቶች መኖራቸውንም የሚጠቅሱ ተመራማሪዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ ሽርማን የተባሉ ተመራማሪ በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ባካሄዱት ጥናት፤ በአዕምሯዊ ተግባራት ረገድ በወንዶችና በሴቶች ተማሪዎች መካከል ምንም ልዩነት አለመኖሩን (አለማግኘቱን) መግለፁንና በሒሳብ ችሎታ ረገድም ከፆታ ልዩነት አኳያ ከግምት ሊገባ የሚችል ልዩነት አለመታየቱን (አለመኖሩን) የሚጠቁሙ ሌሎች የጥናት ግኝቶች መኖራቸውንም Betz and Fitzegerald (1987) ይዘግባሉ፡፡

በጥቅሉ የፆታ ልዩነትንና ትምህርትን አስመልክተው ከተካሄዱ ጥናቶች የምንረዳው በሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ በየትኛውም የትምህርት ደረጃ በየትምህርት ዓይነቱ ወንዶች ተማሪዎች ከሴት ተማሪዎች የተሻለ ውጤት የሚያስመዘግቡ ሲሆን፤ በምዕራባውያኑ ዘንድ ግን የተካሄዱ ጥናቶች

በተለይም በክፍል ፈተናዎች የሴት ተማሪዎች አጠቃላይ ውጤት ከወንድ ተማሪዎች ውጤት የተሻለ ሆኖ እንደሚገኝ ይዘግባሉ (Roson 1989፣ Betz and Fitzgerald 1987፣ Hayiden, Betz and Fitzegerald 1987)

### 2.2.1 የጾታ ልዩነትና የቋንቋ ትምህርት

በቃላዊና ስነልሳናዊ ዘርፎች ከወንዶች ይልቅ ሴት ተማሪዎች የተሻሉ እንደሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ በቴክኒክና ሙያ እንዲሁም በሂሳብ ዘርፎች ወንድ ተማሪዎች ከሴት ተማሪዎችየተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንደቻሉ ወንድና ሴት ተማሪዎች ባላቸው የአዕምሮ ተግባራት ልዩነት ላይ ሰፊና ጥልቅ ጥናት ያደረጉት Macoby.E.E and Jackline C.N (1974) ያስረዳሉ።

Macoby. E.E and Jackline C.N. (1974) የጥናት ውጤት በተቃርኖ Warrik, D. Pamela and Jack.A. Naglieri. (1993) የሀይዲን የጥናት ግኝት ጠቅሰው በቃላዊና ስነልሳናዊ ተግባራትና ዘርፎች በሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል የሚታየው ልዩነት አነስተኛ እንደሆነ ያስረዳሉ። በተጨማሪም Macoby.E.E. and Jackline C.N. (1974) ቃላዊ ተግባራት ብለው ያስቀመጡት ሀረግ የሚያስተላልፈውን ጽንሰ ሀሳብ ግልጽ የሆነ ብያኔና ማብራሪያ በጥናታቸው ላይ ሊሰጡ ባለመቻላቸው የጥናታቸው ውጤት ተቀባይነት ላይ ጥያቄ ያጫረ እንደሆነ Warrik, D. Pamela and Jack.A.Naglieri (1993) በጥናታቸው ጠቅሰውታል።

በተጨማሪም በሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል ባሉት የቋንቋ መልመድ (መማር) ክሂል ረገድ ጥናታቸውን ካካሄዱት ምሁራን መካከል አንዷ Williams, H. Juanita(ed). (1985) እንደገለጸችው የተለያዩ ምሁራን ዕድሜያቸው ከ 9ወር እስከ 12 ዓመት በሚደርስ ወንድ እና ሴት ልጆች መካከል ያካሄዷቸው ጥናቶች አጠቃላይ ሁኔታ በቋንቋ መልመድ (መማር) ረገድ ሴቶች ከወንዶች የተሻሉ ሆነው መገኘታቸውን የሚያሳይ መሆኑን ትገልፃለች።

Williams, H.Juanita (ed) (1985) በጥናት ግኝቷ አያይዛ እንደገለጸችው በማናቸውም የዕድሜ ደረጃ ሴት ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት፣ በቃላት እውቀት መጠን በንባብ ክሂል ወዘተ … ከወንዶች የተሻሉ መሆናቸውን ነው።በሌላ በኩል Olson (1979) በንባብ ክሂል ረገድ በየትኛውም የዕድሜ ክልልላይ የሚገኙ ሴቶች ከወንዶች የተሻሉ ሆነው መገኘታቸውን ይጠቁማል።

በጾታ ልዩነትና በቋንቋ ትምህርት ውጤት መካከል ባለው ልዩነት ሴቶች ከወንዶች ቀድመው አቅመ ንባባቸው ስለሚጎለብትና ገና ህጻን እያሉ ማናበብና መጻፍን ይለምዳሉ (Balair 1988)። የባሊየር ሀሳብ በሌሎች ምሁራን በጾታ ልዩነትና በቋንቋ ትምህርት ክሂል ችሎታ ዙሪያ የተሰነዘሩ ሀሳቦችን የሚያጠናክር ነው።

ከነዚህ ምሁራን መካከል Piyanu Kool, S. (2001) እንደጠቆሙት፤ ወንድም ይሁን ሴት ተማሪዎች ወደትምህርት ቤት ሲገቡ ለትምህርት ያላቸው ዝንባሌ ተመሳሳይ ነው።ቆየት ብሎ ግን የሁለቱም ዕድሜያቸው እየገፋ የክፍል ደረጃቸውም እየጨመረ ሲሄድ ንባብ የሴቶች ተግባር ብቻ እንደሆነ አድርገው Piyanu Kool, S. (2001) ይገምታሉ። በሌላ በኩልበትምህርት ቤት ውስጥ በሚደረግ ንባብ በ10ና በ12 ዓመት መካከል የሚገኙ ሴት ተማሪዎች ከወንድ አቻዎቻቸው በተሻለእንደሚያዘወትሩ በተደረገ የክፍል ምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል።
በሌላ ጥናት Balair, H. and Sanford,K. (1999) እንደጠቆሙት ወንዶች የሚያነቡት የሚያስደስታቸውን ሲሆን አሰልቺነት ያላቸውን ትምህርቶች መማርም ሆነ ማንበብ አይፈልጉም። አብዛኞቹ ወንዶች ትኩረት በስፖርት፣ በኤሌክትሮኒክስ፣ በድህረገጽ ጨዋታዎችና በጋዜጣ የሚወጡ ፅሑፎችን በማንበብ ረገድአብዛኞቹ ወንዶች ከሴቶች በተለየ ትኩረት ያደርጋሉ። አጥኚዎቹ አያይዘው ሲያብራሩ ይህ የፆታ ልዩነት በትምህርት ውጤት ላይ ልዩነት የሚያመጣ መሆኑን አመላካች ነው። ይህም ሴቶች ከወንዶች በተሻለ ለቆሙለት አላማ ትኩረት እንደሚሰጡና ጽንሰ ሃሳባዊ ለሆኑ ይዘቶች ዝንባሌ እንዳላቸው ያመላክታል፤ጨምረው እንደገለፁት በክፍል ውስጥ መምህሩ የሚመርጣቸው የንባብ ጽሁፎች ተግባራትና ርዕሰ ጉዳዮች ለሁለቱም ፆታዎች ሳቢ የሆኑና መተግበር የሚችሉ መሆን አለባቸው። አጥኚዎቹም አክለው ለወንድና ለሴት ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት የሚያነቡትን እንዲመርጡ እድል መስጠት በትምህርታቸው ላይ አዎንታዊ የሆነ ስሜት ይፈጥራል፤ የትምህርት ውጤታቸውም ይጨምራል።

ሌላው ከዚህ ጋር በተያያዘ Gentry, J.L. (2000) ኪሎግ (1995)ን ዋቢ አድርገው እንደገለፁት አንብቦ መረዳት ከፆታ አንፃር ልዩነት እንዳለው በተሰሩ ጥናቶች ላይ ባደረጉት ቅኝት በሴቶችና በወንዶች መካከል ልዩነት የሚታይ መሆኑን ቢጠቁሙም የጐላ ባለመሆኑ ከልዩነታቸው ይልቅ ተመሳስሏቸው ይበልጣል ወደሚል ድምዳሜ ደርሰዋል በተቃራኒው Gentry, J.L. (2006) የቴክስት አወቃቀር ትምህርት በአራተኛ ክፍል ተማሪዎች የቃላት አወቃቀር አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ያለው ተፅዕኖ በሚል ርዕስ ባካሄዱት ጥናት በአንብቦ መረዳት ችሎታ ሴቶች ከወንዶች ጉልህ ልዩነት እንዳሳዩና የበለጠ ውጤት ማምጣታቸውን አመላክተዋል።

አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በቋንቋ መልመድ ረገድ ሴቶች ከወንዶች የበለጡ መሆናቸውን ነው።ከነዚህ ጥናቶች ውስጥ ለምሳሌ ያህል Betz, Nancy and Louise. F. Fitzegerald (1987) ሴት ልጆች ከወንድ ልጆች ቀድመው አፋቸውን እንደሚፈቱ ሲጠቁሙ

Williams, H. Juanita (ed) (1985) ደግሞ በቋንቋ መማር (መልመድ) ረገድ ሴት ከወንድ በእጅጉ ትፈጥናለች ብለው ይተነትናሉ።

በተጨማሪም እነዚህ ተመራማሪዎች ሴቶች የተሻለ የቋንቋ ችሎታ ሊኖራቸው የቻለው ምናልባት ሴቶች ከወንዶች የበለጠ ተናጋሪ ናቸው ከሚለው አመለካከት በመነሳት ወላጆች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ከወንዶች ልጆቻቸው ይልቅ ከሴቶች ልጆቻቸው ጋር መነጋገር ስለሚያዘወትሩና፣ ይህም በበኩሉ የሴት ህፃናትን የቋንቋ ችሎታ በማዳበር ረገድ አስተዋጽኦ ሊያደርግ በመቻሉ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል የሚዘግቡ ጥናቶች መኖራቸውን ይገልፃሉ።

Hughes, Sunderland (1994) እንዲሁም Clark, Ann and Trafford. (1995) ከላይ በተጠቀሱት አጥኚዎች የቀረቡትን የጥናት ውጤቶች ሀሳብ የሚጋሩ ሲሆን በዘመናዊ ቋንቋዎች ትምህርት አኳያም ሴቶች ከወንዶች የተሻሉ ሆነው መገኘታቸውን ይጠቁማሉ።በተጨማሪም Johnes, L. and T. smart (1995) ተማሪዎች እድሜያቸው እየጨመረ በሚሄድበት ጊዜ እንደ ሒሳብ ና ሳይንስ ከመሳሰሉ የትምህርት ዓይነቶች ይልቅ፣ ለዘመናዊ ቋንቋ የሚኖራቸው ዝንባሌ እንደሚጨምር የተለያዩ ተሞክሮዎችን በመጥቀስ ያስረዳሉ።

ከላይ ከተጠቀሱት የዘርፉ ምሁራን በተጨማሪም Cameron, (1985) ባቀረበችው ጥናት ከፍ ብለው በተጠቀሱት ምሁራን የቀረበውን የጥናት ውጤት ትሞግታለች። ምሁሯ ምክኒያቷን ስታቀርብ በዚህ ረገድ ለሚታይ የፆታ ልዩነት በቂ ማረጋገጫ አለመኖሩን በመጠቆም ነው።

እንግዲህ ከላይ በስፋት ከተዘረዘሩትና በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ አጥኚዎች ከቀረቡት የጥናት ውጤቶች ለመረዳት እንደሚቻለው በቋንቋ ትምህርት ክሂል ረገድ በወንድና ሴት ጾታ መካከል የተወሰነ ልዩነት እንዳለ ነው።

## 2.4. ሴትና ወንድ ተማሪዎች በትምህርት ረገድ ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት

በጾታ ልዩነትና ትምህርት ዙሪያ ጥናታቸውን ያካሄዱ የተለያዩ ምሁራን በትምህርት ረገድ ሴትና ወንድ ተማሪዎች ባላቸው በራስ የመተማመን ጥንካሬ ልዩነት እንዳለ ያስረግጣሉ።

ከነዚህም ምሁራን መካከል Betz, Nancy and Louise. F. Fitzegerald. (1987) እንደገለጹት ሴት ተማሪዎች ከወንድ አቻዎቻቸው በተቃራኒ ለራሳቸው ችሎታና ተሳትፎ የሚሰጡት ግምት እንዲሁም ከተግባራቸው የሚጠብቁት ውጤት አናሳ ነው። እንደ ምሁራኑ ገለጻ ከሆነ ይህ የሚከሰተው ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ባሉ የትምህርት ተቋማት ሲሆን ለራስ አናሳ ግምት መስጠት የሚስተዋለው ከወንዶች ያነሰ ችሎታና ተሳትፎ ባላቸው ብቻ ሳይሆን ተመጣጣኝ አለያም ላቅ ያለ ችሎታና ውጤት ባላቸው ሴት ተማሪዎች ጭምር ነው።

Macoby E.E and Jackline C.N (1974) በጥናታቸው በነ Betz, Nancy and Louise. F. Fitzegerald. (1987) የተጠናውን ጥናት ውጤት የሚያጠናክር ሃሳብ ሲሆን ሴቶች በተለይም ወንዶች የተሻለ ውጤት ያስመዘግባሉ ተብሎ በሚታመንባቸው እንደ ሂሳብና ሳይንስ በመሳሰሉ የትምህርት ዓይነቶች ረገድ ያላቸው በራስ የመተማመን ስሜት ዝቅተኛ መሆኑን ይጠቁማሉ።
በሌላ ጥናትLott, Bernice. (1987)ቀደም ብለው በተጠቀሱት አጥኚዎች የቀረቡትን የጥናት ውጤቶች የሚደግፍ የጥናት ውጤት ያቀረበች ሲሆንከአራተኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል በሚማሩ ተማሪዎች ላይ በተካሄደ ጥናቷ ሴቶች በአብዛኛው የትምህርት ዓይነቶች ለሚያስመዘግቡት ውጤት ያላቸው የራስ ግምት ከወንድ ተማሪዎች አኳያ ሲታይ ዝቅተኛ መሆኑን ጠቁማለች። በተጨማሪም በተመሳሳይ የክፍል ደረጃ ላይ በተካሄደ ጥናት በሂሳብ ችሎታቸውና በቋንቋ ፊደላት ዕውቀታቸው ወንድ ተማሪዎች ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት ከሴት ተማሪዎች አኳያ የተሻለ መሆኑን ገልጻለች።
ከዚሁ ጋር ተያይዞ Johnes, L. and T. smart. (1995) እንደዘገቡት ሴትና ወንድ ተማሪዎች ለራሳቸው የሚኖራቸው አመለካከት መለያየት ከሚያከናውኑት ተግባራት ስኬት አለያም ውድቀት ጋር ተያያዥነት እንዳለው ጠቁመው ሴቶች ባከናወኑት ተግባር ስኬታማ ካልሆኑ ለውድቀታቸው መንስዔው የችሎታቸው ዝቅተኛነት መሆኑን ወደማመኑ ሲያደሉ በተቃራኒው ደግሞ ወንዶች በቂ ጥረት ባለማድረጋቸው ምክኒያት መሆኑን ያምናሉ ሲሉ ያስረዳሉ።
Betz, Nancy and Louise. F. Fitzegerald (1987) ከላይ የቀረበውን ሀሳብ ሲያጠናክሩ ሴት ተማሪዎች ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት ለሚኖራቸው ዝቅተኛ ተሳትፎና ለሚያስመዘግቡት በቂ ያልሆነ ውጤት መሰረታዊ ምክንያት ከመሆን በዘለለ ለቀጣይ ህይወታቸው መሳካት ተግዳሮት ሊሆን ይችላል በማለት ይገልጻሉ።
ባጠቃላይ ከላይ በዝርዝር ከቀረቡት የጥናት ውጤቶች ለመረዳት እንደሚቻለው ሴትና ወንድ በተፈጥሮ ያገኙት የአመለካከት ልዩነት ባይኖርም ከተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች በሚነሱ ልዩነቶች ሳቢያ በሁለቱ ጾታዎች መካከል ልዩነት ይስተዋላል። ልዩነት ከሚስተዋልባቸው ዘርፎች መካከል በዋንኛነት ሴትና ወንድ ተማሪዎች በትምህርት ረገድ ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት ሲሆን ሴት ተማሪዎች ከወንድ አቻዎቻቸው አንጻር ለራሳቸው አናሳ ግምት ይሰጣሉ። ይሁን እንጂ የተወሰኑ የጥናት ውጤቶች በሁለቱ ጾታዎች መካከል የጎላ ልዩነት እንደሌለ ያስረዳሉ።

## 2.5. የተቀናጁ ሙከራዎች (Integrative Tests)

Carroll, Johan B (1961) እንደሚገልጸው የቋንቋ ሙከራዎች ዋና ዓላማ የተማሪውን የቋንቋ ዕውቀት እና ችሎታ ለመወሰን አለያም አንድ ተማሪ ከሌሎች ተማሪዎች አንጻር ያለውን የቋንቋ ችሎታ ልዩነት ለማሳየት ነው።

ቅንጁ ሙከራዎች፤ Hughes, A. (1989)፤ ተማሪው አንድን የቋንቋ መልመጃ ለማጠናቀቅ የተለያዩ የቋንቋ ክሂሎችን ወይም የተማሪውን የቋንቋ ብቃትን በማቀናጀት እንዲጠቀም የሚያደርግ የሙከራ ዓይነት ነው በማለት ብያኔ ይሰጣሉ።በሌላ አገላለጽ ቅንጁ ሙከራዎች የሚመዝኑት ቋንቋን በተናጠል ሳይሆን በጥቅሉ ነው። በተጨማሪም ቅንጁ ሙከራዎች ተማሪዎች በአንድ የቋንቋ ቅንጣት ላይ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ስነልሳናዊ ውሁዶችን እንዲያጣምሩ የሚያደርጉ የሙከራ ዓይነቶች ናቸው።

ቅንጁ ሙከራዎች የቋንቋ ተማሪው በተለያየ ማህበራዊ ዐውድ ውስጥ በተለየ ሁኔታና ጊዜ ቋንቋውን በትክክል መጠቀም መቻሉንና አለመቻሉን በመለካት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸው Patricia, I እና ሌሎች (1974) ሲገልፁ፤Oller, Jr. (1972) የቅንጁ ሙከራዎችቀደምት የሆኑና ትኩረታቸውም በተማሪው አጠቃላይ ተግባቦታዊ ችሎታ ላይ መሆኑን ይዘግባል።

ቅንጁ የቋንቋ ሙከራዎች የተማሪዎችን እያንዳንዱን የቋንቋ ክሂል በተናጠል ለመለካት ከሚሞክሩት የቋንቋ ሙከራዎችበዋንኛነት የሚለዩት ተማሪዎችየተለያዩና ብዛት ያላቸውን የቋንቋክሂሎችን በማቀናጀት ለመጠቀም ያላቸውን ችሎታ ለመመዘን የሚያስችሉ በመሆናቸው ነው።ከዚህ ጋር ተያይዞ Oller (1979) እንደሚጠቁመው የቅንጁ ሙከራዎች ትኩረት ተማሪው ቋንቋውን የሚማርበት ዓላማ ምንም ይሁን ምን ተማሪው ይኖረዋል ተብሎ በሚታመነው ውስጣዊ የቋንቋ ችሎታ ላይ ተመርኩዞ ነው።

እንደ Hegnes, A. (1989) አገላለጽ የተቀናጁ ሙከራዎች የሚባሉት የግንዛቤ መለያ ሙከራ (Cloze Test)እና የቃል ጽህፈት (Dictation) ናቸው።

በመሆኑም በዚህ የጥናት ሥራ ውስጥ አጥኚዋ የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂል ችሎታ ከጾታ ልዩነት አኳያ ለመመዘን የመስኩ ባለሙያዎች የቅንጁ ሙከራ ዓይነቶች ብለው ከሚጠሯቸው የግንዛቤ መለያ ሙከራ (Cloze Test)እና የቃል ጽህፈት (Dictation)ተገቢ በመሆናቸው ለመጠቀም ወስናለች።

### 2.5.1. የግንዛቤ መለያ ሙከራ

የግንዛቤ መለያ ሙከራን አንድምታና የቋንቋ ብቃትን ከመለካት አንጻር ያለውን ጠቀሜታ በተመለከተ የተለያዩ የቋንቋ ምሁራን በተለያዩ ጊዜያት ያቀረቧቸውን ጽሁፎች በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

እንደ Davies, A. (1988)፤ Oller,J, Jr (1979) እንዲሁም Weir, Cyril. (1990) አገላለጽ ከሆነ የግንዛቤ መለያ ሙከራ የአንድን ጽሁፍ ተነባቢነት ከሁለገብ አንብቦ መረዳት አንጻር፤ የቋንቋውን አጠቃላይ ችሎታና ብቃት ለመገመት እንዲሁም አውዳዊተግዳሮቶችን ለመፈተሽ ያገለግላል፡፡ Taylor, D. (1953) በበኩሉ የግንዛቤ መለያ ሙከራዎች የጽሁፎችን ተነባቢነት ለመተንተን የሚያገለግል መሳሪያ ነው በማለት ብያኔ ይሰጣል፡፡

Taylor አክሎም ለግንዛቤ መለያ ሙከራ ብያኔ ሲሰጥ የግንዛቤ መለያ ሙከራ በአንድ ምንባብ ውስጥ ከሚገኙ ቃላት መካከል እያንዳንዱን ቃል በመግደፍ ተፈታኙ ጠቅላላ ጽሁፉ ከሚጠቀመው አውዳዊ ፍቺ በመነሳት በተገደፈው ቃል ቦታ ተስማሚ ይሆናል ብሎ የሚያስበውን ቃል ተክቶ ፅሑፉ የተሟላ ሃሳብ እንዲኖረው የሚያደርግበት ስልት ነው በማለት ያስረዳል፡፡

ሌላው በዘርፉ ጥናት ካደረጉ ምሁራን መካከል አንዱ የሆነው Oller,J, Jr (1979) እንደገለጸው የግንዛቤ መለያ ሙከራዎች የሚከተሉት ሂደት በቅድሚያ የጽሁፉን የተነባቢነት ሁኔታ መተንተን ሲሆን በመቀጠልም ይህንን ጽሁፍ ተጠቅሞ የተማሪውን አንብቦ የመረዳትችሎታ መመዘን ይሆናል፡፡

የግንዛቤ መለያ ሙከራ፤ Oller,J, Jr (1973)፤ አንድ ምዘና ወሳጅ ያልተሟላ መረጃን መሰረት አድርጎ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች ተስማሚ ቃላትን ወይም ሀረጋትን በመሙላት ምንባቡ የተሟላ ሀሳብ እንዲሰጥ ለማድረግ የሚያስችል፤ የተመዛኙን የንባብ ችሎታ እንዲሁም የተለያዩ የቋንቋ ክህሎቶችን እንዲያዳብር የሚያደርግ በተጨማሪም የቋንቋ ብቃትን በመመዘን አንጻር አስተማማኝና ትክክለኛመመዘኛ መሳሪያ ከመሆኑም በላይ ለአዘገጃጀትም ሆነ ለአቀራረብ አመቺ መሆኑን ይጠቅሳል፡፡

በተለያዩ ማህበራዊ ዐውዶች ውስጥ ቋንቋን በተገቢው መንገድ የመጠቀም ችሎታን ጨምሮ የተመዛኙን አጠቃቀላይ ስነ-ልሳናዊ ችሎታ ለመረዳት የሚያስችል ጠቃሚ የቋንቋ መመዘኛ ነው፡፡ በተጨማሪም በማዳመጥ በመጻፍና በመናገር ክሂሎች መካከል ጠንካራ የሆነ አዎንታዊ ቁርኝት እንዳለ የተለያዩ ጥናቶች ይጠቁማሉ በማለት Heaton,J. (1988) ይገልጻል፡፡

Tebebe (1987) ኒውማንን ጠቅሶ እንደገለጸው የግንዛቤ መለያ ሙከራ የአንድን ተመዛኝ የንባብ ችሎታ ዝርዝር ሀሳቦችን ከአጠቃላይ ሀሳቦች ለመለየት ያለውን ብቃት ከአንድ የተወሰነ ፍንጭ

በመነሳት ውጤትን ለመተንበይ ያለውን አቅምና ከተወሰኑ ቁንጽል ሀሳቦች ተነስቶ አንድ የማጠቃለያ ሀሳብ ላይ ለመድረስ ያለውን ችሎታ ለመገምገም ያስችላል፡፡

እንደዘርፉ ምሁራን ከሆነ ግንዛቤ መለያ ሙከራዎችን ለማረምና ውጤት ለመስጠት ሁለት ዓይነት የአስተራረም ዘዴዎችን ልንጠቀም እንችላለን በማለት ያስረዳሉ፡፡ እነሱም፡ የተለመደው (ነባር) ቃል አስተራረም ዘዴና የተመሳሳይ ቃል አስተራረም ዘዴዎች ናቸው፡፡

የተለመደው ወይም የትክክለኛው ቃል አስተራረም ዘዴ ተመዛኙ ትክክለኛውን ወይም ዋናውን ቃል እንዲጠቀም የሚያደርግ ሲሆን በሌላ በኩል የተመሳሳይ ቃል አስተራረም ዘዴ ደግሞ ተመዛኙ ተቀባይነት ወይም ተገቢነት ያለው ተመሳሳይ ቃል እንዲጠቀም ያስችለዋል፡፡

በአጠቃላይ ከፍ ብሎ የተለያዩ ምሁራን ለማስረዳት እንደሞከሩት የግንዛቤ መለያ ሙከራ የአንድን ተመዛኝ የቋንቋ ክሂሎቶቹን ብቃት ለመመዘን የተሻለ፤ አመቺና ሁሉን አቀፍ የምዘና ዘዴ እንደሆነ ነው፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢም የግንዛቤ መለያ ሙከራ በተገቢው መንገድ በስራ ላይ ካዋሉት የተመዛኙን የቋንቋ ብቃትን በመለካት ረገድ ተመራጭና አስተማማኝ ዘዴ እንደሆነ ታምናለች፡፡

#### 2.5.1.1. የግንዛቤ ሙከራዎች ጠንካራና ደካማ ጎኖች

የግንዛቤ መለያ ሙከራዎች የሚከተሉት ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉት

##### *2.5.1.1.1. ጠንካራ ጎኖች*

- ትኩረት የሚያደርጉት ቋንቋን ለተግባቦት ዓላማበትክክል መጠቀም ላይ ነው፡፡
- ሁሉንም የቋንቋ ውሁዶች አጣምሮ ቋንቋን ለመጠቀም ያስችላል፡፡
- ምርጫ ሰጪ የሆኑ የፈተና ዓይነቶች በግምት መልስ የማግኘት አጋጣሚን ይቀንሳል ወይም ያስወግዳል፡፡
- አጠቃላይ የቋንቋ ብቃትን በመለካት ረገድ አስተማማኝ የመመዘኛ ዘዴ ነው፡፡

##### *2.5.1.1.2. ደካማ ጎኖች*

- ግልጽ፤ ትርጉም ያለውና አካታች መመዘኛ መስፈርት ለማስቀመጥ ያስቸግራል፡፡
- በተመዛኞች ያለው ተቀባይነት አነስተኛ ነው፡፡

#### 2.5.2.የቃል ጽህፈት ሙከራ

የቃል ጽህፈት ሙከራ ከቅንጁ ሙከራዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ Oller,J. Jr (1972፣ 1979)፣ Patricia, l (1974)፤ Heton,J. (1979)፣ Fouley,K (1985) በጥናታቸው ከቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ አንዱ የሆነው የቃል ፅህፈት ሙከራ አጠቃላይ የቋንቋ ክሂል ችሎታን በመለካት ረገድ አስተማማኝና ትክክለኛ መለኪያ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ምሁራኑ አክለውም የቃል ጽህፈት ሙከራ አንፃራዊ በሆነ መልኩ በአዘገጃጀትም ሆነ በአቀራረብ ረገድ ቀላልና አመቺ መሆኑንም ይጠቁማሉ፡፡

የቃል ፅህፈት ሙከራ በአብዛኛው እንደሚታመነው አንድን ምንባብ አዳምጦ ቃል በቃል በፅሁፍ ማስፈር ብቻ ሳይሆን ከዚህ ላቅ ያለ የቋንቋ ችሎታን የሚጠይቅ ተግባር ነው፡፡ የቃል ፅህፈት ሙከራ ከአንድ በላይ የቋንቋ ክሂሎችን ለመለካት የሚያስችል የቋንቋ ሙከራ ነው፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ Mackey (1965) and Heton (1975) እንደገለጹት አንድ ተፈታኝ ለቃል ጽህፈት ፈተና በሚቀመጥበት ወቅት ፊደላትንና ቃላትን የመለየት ችሎታን፣ የመፃፍና የነጥብ አጠቃቀም ችሎታውንና ያዳመጠውን አገናዝቦ የተወሰነ ትርጉም የመስጠት ችሎታውንና የመሳሰሉትን የቋንቋ ክሂሎቹን መጠቀም እንደሚኖርበት እንዲሁም አዳምጦ የመለየትን፣ አዳምጦ የማስታወስን፣የድምፆችን ቅደም ተከተላዊ አሰላለፍ ማስታወስን፣ የስፔሊንግ ችሎታውን፣ የቋንቋውን ሰዋሰዋዊና ቃላዊ ስርዓት እውቀቱን እና የመሳሰሉትን ቅንጁ የቋንቋ ክሂሎቹን መገልገል እንደሚገባው ነው፡፡

የቃል ጽህፈት የቋንቋ ብቃትን ከመለካት አንጻር ያለውን ተገቢነት በተመለከተ የተለያዩ ጥናቶች በተለያዩ ጊዜያት ተከናውነዋል፡፡ከነዛ ውስጥ Oller(1971) እንግሊዝኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩ 100 ተማሪዎች ላይ ባካሄደው ጥናት የቃል ጽህፈትን ጨምሮ ቃላትና አንብቦ መረዳትን ትክክለኛውን መልስ መምረጥና ድምጾችን ለይቶ ማወቅን ያካተተ መደበኛ ፈተና በማቅረብ በፈተናው የተለያዩ ክፍሎች መካከል አንዱ ከሌላው ያለውን ተዛምዶ ለማየት ሞክሯል፡፡ የጥናቱ ውጤት የሚያሳየው የቃል ጽህፈት ከሌሎቹ የፈተና ዓይነቶች በተሻለ ከእያንዳንዱ የፈተና ዓይነት ጋር ከፍተኛ ተዛምዶ እንዳለው ነው፡፡ Oller አክሎ ሲያስረዳ የቃል ጽህፈት የተለያዩ የቋንቋ ክሂሎችን ለመመዘን የሚያስችል የቋንቋ ሙከራ መሆኑን ገልጿል፡፡

የዚህ ጥናት አቅራቢ ቀደም ብለው የተጠቀሱት ምሁራን የቃል ጽሁፍ የቋንቋን ችሎታ ከመመዘን አኳያ ያለውን ጠቀሜታ የዘረዘሯቸውን ነጥቦች የምትጋራ ሲሆን ለዚህ ጥናት ከተጠኝዎቹ መረጃ ለመሰብሰብ ተስማሚ ነው ብላ ታምናለች፡፡

### *2.5.2.1.የቃል ጽህፈት ጠንካራና ደካማ ጎኖች*

የቃል ጽህፈት የሚከተሉት ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉት

### *2.5.2.2.ጠንካራ ጎኖች*

- ከሌሎች የምዘና ዓይነቶች አንጻር የቃል ጽህፈት ለአዘገጃጀትና ለአቀራረብ ቀላልና ጊዜ ቆጣቢ ነው::
- የተመዛኙን የአጭር ጊዜ ትውስታ ከመመዘን አንጻር አስተማማኝና ትክክለኛ የቋንቋ ብቃት መለኪያ ነው::

### *2.5.2.3.ደካማ ጎኖች*

- የቃል ጽህፈት መመዘኛ ሆኖ የሚቀርበውን ምንባብ የክብደት ደረጃ ለመወሰን አስቸጋሪ መሆኑ::
- በምዘናው ወቅት ተመዛኙ በአንድ ጊዜ አዳምጦ የሚጽፈውን የምንባቡን ክፍል ከተማሪው ችሎታ አንጻር ለመከፋፈል አስቸጋሪ ሊሆን መቻሉ::

## 2.5.የቃል ፅህፈትና የክሂል ዘርፎች ትስስር

የቃል ፅህፈት ለሙከራ ተግባር እንዲውል ካበቁት ጉዳዮች ዋነኛው አብዛኞቹ የክሂል ዘርፎች የሚጠይቁትን ልምምድ አቀናጅቶ የማቅረብ አቅም ያለው መሆኑ ነው (Stansfield፣1985):: በተለይም ከአዳምጦ መረዳት ፣ አሳብን በፅሁፍ ከመግለፅና ከስነ-አገባብ ችሎታ ጋር ጥብቅ ዝምድና የሚታይበት ሲሆን፤ከነዚህ ዘርፎች ጋር ተዛምዶ ያላቸውን አዕምሯዊ ክንውኖች በማነቃቃትና የፈጠራ ችሎታን በማነሳሳት ረገድም የማይናቅ አስተዋፅኦ ያበረክታል:: የሚከተለው ዝርዝር ሀሳብ ይህንን መነሻ ያጠናክርልናል::

የቃል ፅህፈት ጎላ ባለ ድምፅ፣በሚነበብ ፅሁፍ አማካይነት የሚተገበር በመሆኑ ተማሪዎቹ መምህሩ በሚያንብበት ጊዜ ሊከሰቱ የሚችሉትን ጥቃቅን መሰናክሎች ተቋቁመው መልዕክቱን ለመረዳት ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል (Anderwood1989):: በተመሳሳይ መምህሩ ሊፈጥን ወይም ሊያዘግም ስለሚችል ከዘወትራዊው የማዳመጥ ስልት ለየት ያለ ችሎታ ማስፈለጉ አይቀሬ ጉዳይ ነው:: ተማሪዎች ይህን ችሎታ እንዲያዳብሩ በማድረግም ረገድ የቃል ፅህፈት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው (Stanfield1985)::

ያዳመጡትን የሚገነዘቡት በምንባቡ ውስጥ የተካተቱትን ቃላት አገባባዊ ሚና አጢነው ቋንቋው በሚፈቅደው የአርፍተ ነገር አገነባብ እየተመሩ ሰፋፊ ቅንጅቶችን ወደ ትርጉም አዘል አሀዶች ሸንሽነው በፈርጅ በፈርጃቸው ማስተንተን ሲችሉ በመሆኑ የቃል ፅህፈት ይህን አእምሯዊ ክንውን ለማለማመድ ይረዳል(Oller1971)::የእምቅ ሀሳቦችን መልዕክት ለመረዳት የሚረዷቸውን አበይት

ነጥቦች ነጥሎ ለማውጣት ለሚያደረጉት ጥረት አትኩሮታዊ ማዳመጥን (intensive listening) እንዲለማመዱ ማገዙም ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚታይ ሌላው የቃል ፅህፈት ሚና ነው(Morris1983)፡፡

በሌላ በኩል አዳምጦ መረዳት የሚቻለው በተመጠነ የጊዜ ቅንብብ ውስጥ በመሆኑ መልዕክትን በፍጥነት ተቀብሎ ለማስተላለፍ አስፈላጊ መሆኑ ይታወቃል ፡፡ ይህን ማድረግ የሚቻለውም የአጭር ጊዜ ትውስታ ችሎታ ሲኖር ነው፡፡ በቃል ፅህፈት ትግበራ ወቅት መምህሩ በእያንዳንዱ ትርጉም አዘል አሀድ መካከል ሊኖር የሚገባውን የቆምታ ጊዜ በመመጠን ስለሚያነብ ተሳታፊዎች የእያንዳንዱን አሀድ መልዕክት አስታውሰው በተገቢው ጊዜ ለመፃፍ በሚያደርጉት ጥረት ይህንን ችሎታ ያዳብራሉ (Oller 1979፣ Nation 1991)፡፡

የቃል ጽህፈት ለአዳምጦ መረዳት ከፍተኛ እገዛ የሚያደርገውን አእምሯዊ የሰዋሰው ችሎታ አነቃቅቶ በተግባር እንዲውል የማድረግ አቅምም አለው፡፡ ይኸውም ተማሪው የሚነበብለትን ፅሁፍ መልዕክት መረዳት ይችል ዘንድ ትርጉም አዘል አሃዶች በተናጠልም ሆነ ርስ በርስ ተሳስረው ስለምን እንደሚያወሱ በቅድሚያ መላምት መሰንዘር ይጠበቅበታል፤ ይህ አእምሯዊ ክንውን በትንተና ግንዘባ (analysis by synthesis) ይባላል፤(Oller and Strife1975 , Weir 1990)፡፡

## 2.6..ፎግኢንዴክስ

ከዳል እና ቻል (Dall and Chall) ፣ ስፖች (Spach) ፣ ዘ ፍራይግራፍ (The Fry Graph)፣ ዘ ፍላሽ ፎርሙላ (The Flash Formula) በተጨማሪ ፎግኢንዴክስ (Fog Index) አንድ ጽሁፍ ያለውን የተነባቢነት ደረጃ (Readability) ደረጃ ለመለካት ወይም ለመገመት የሚያስችል የተነባቢነት ቀመር ነው፡፡

የተነባቢነት ደረጃ መመዘኛዎች በስፋት መጠቀም የተጀመረው በ1900ዎቹ መጨረሻ ላይ ነው፡፡ ከነዚህ መመዘኛዎች ውስጥ አንዱ ፎግ ኢንዴክስ ነው፡፡ ፎግ ኢንዴክስ በ1960ዎቹ በሮበርት ገኒንግ ዲዛይን የተደረገ ነው፡፡ በ1952 ገኒንግ "The Technique of Clear Writing" የተሰኘ መጽሀፍ ለህትመት ያበቃ ሲሆን መጽሀፉም ፎግ ኢነዴክስን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል በዝርዝር ያሳየ ነበር፡፡

በአንድ የተወሰነ ደረጃ ላይ ለሚገኝ ፅሁፍና አማካይ አንባቢ ይኖረዋል ተብሎ የሚገመተውን ምንባብ አንብቦ የመረዳት ችሎታን መሰረት በማድረግ፤ የአንድን ፅሑፍ የተነባቢነት የክብደት ደረጃ ለመገመት የሚያስችል ቀመር ፎግ ኢንዴክስ ይባላል፡፡መሰረት አድርጎ የተነሳበት መነሻ ሃሳቡ ረጃጅም ዓረፍተነገሮች ከአጫጭሮቹ እንዲሁም ሶስትና ከዚያ በላይ ቀለሞች (syllable) ያላቸው ቃላት ከእነዚህ ከሚያንሱት ይልቅ ለመረዳት አስቸጋሪ ናቸው፤ የሚል ድምዳሜ ነው፡፡

ይህንኑ የተነባቢነት የክብደት ደረጃ ቀመር መሰረት በማድረግ በዚህ ጥናት ላይ የተማሪዎቹን የቋንቋ ክሂል ችሎታ ለመለካት የተመረጡ የቃል ፅህፈት ሙከራና የግንዛቤ መለያ ሙከራ ምንባቦች ተሳታፊዎች ለተመረጡበት የክፍል ደረጃ (ለ9ኛ ክፍል) የሚመጥኑ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

ይህ ቀመር ተመሳሳይ የሆነ ግልጋሎት ከሚሰጡት ሌሎች የተነባቢነት የክብደት ደረጃ ቀመሮች መካከል በአጥኚዋ የተመረጠበት ዋነኛ ምክንያት፣ ውስብስብ የሆነ የሒሳብ ስሌትን የማይጠይቅና ለአሰራር ቀላልና አመቺ በመሆኑ ነው፡፡

ለአንድ የተወሰነ የክፍል ደረጃ የሚመጥን የተነባቢነት ክብደት ደረጃ ያለውን ምንባብ ለመምረጥ የሚከተሉት ተግባራት በቀደም ተከተል መከናወን ይኖርባቸዋል በማለት Jilliland (1975) ይዘረዝራል፡፡

ሀ. ከአንድ ረጅም ፅሑፍ ውስጥ የተወሰኑ ቃላት ያሉት ምንባብ መምረጥ፣

ለ. በተመረጠው ምንባብ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት ብዛት ማወቅ፣

ሐ. በተመረጠው ምንባብ ውስጥ የሚገኙትን አረፍተ ነገሮች ብዛት ማወቅ፣

መ. በምንባቡ ውስጥ የሚገኙትን አረፍተ ነገሮች አማካይ ርዝመት ለመረዳት በምንባቡ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት ቁጥር በምንባቡ ውስጥ ለሚገኙት አረፍተነገሮች ቁጥር ማካፈል፣

ሠ. በምንባቡ ውስጥ የሚገኙትን ሶስትና ከዚያ በላይ ቀለም ያላቸውን 'ከባድ' ቃላት ብዛት ማወቅ፣ አንድ ቃል በተደጋጋሚ በምንባቡ ውስጥ ከታየ የሚቆጠረው አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡

ረ. የዓረፍተ ነገሮችን አማካይ ርዝመት ስሌት በ ('መ') የተመለከተውን በምንባቡ ውስጥ ከተገኙት ሶስትና ከዚያ በላይ ቀለም ካላቸው ቃላት ቁጥር(በ "ሠ")ከተመለከተው ጋር መደመር፣

ሰ. በመጨረሻም በ ('ረ') የተመለከተውን ድምር ውጤት በ 0.4 ማባዛት፡-

በዚህ ሁኔታ ተሰልቶ የሚገኘው የመጨረሻ ውጤት፣ የተመረጠው ምንባብ ለየትኛው የክፍል ደረጃ እንደሚመጥን የሚያመለክት ይሆናል፡፡

የፎግ ኢንዴክስ ቀመር ይህንን ይመስላል፡፡

ውጤት= 0.4(አማካይ የአረፍተነገር ርዝመት + በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ ከባድ ቃላት)

- አማካይ የአረፍተነገር ርዝመት የሚገኘው በምንባቡ ውስጥ የሚገኙትን አጠቃላይ ቃላት ለአጠቃላይ የአረፍተነገር ብዛት በማካፈል ነው፡፡
- በምንባቡ ውስጥ የሚገኙት ከባድ ቃላት የሚባሉት በናሙናነት በተመረጠው ምንባብ ውስጥ ሶስትና ከዛ በላይ ቀለም ያላቸው ናቸው፡፡

ሰንጠረዥ 1፡ የጉኒንግ ፎግ ኢንዴክስ(Gunnings Fog index)

| የክፍል ደረጃ | የትምህርት ደረጃ | መረዳት |
|---|---|---|
| ከ0 እስከ 5 | 5ኛ ክፍልና ከዚያ በታች | ለመረዳት በጣም ቀላል |
| 6 | 6ኛ ክፍል | ለመረዳት ቀላል |
| 7 | 7ኛ ክፍል | በተወሰነ መልኩ ለመረዳት ቀላል |
| 8 | 8ኛ ክፍል | መካከለኛ |
| ከ9 እስከ 12 | 9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል | በተወሰነ መልኩ ለመረዳት አስቸጋሪ |
| ከ13 እስከ 16 | ኮሌጅ ጀማሪ እስከ ጨራሽ | ለመረዳት አስቸጋሪ |
| 17 | ኮሌጅ ያጠናቀቀ | ለመረዳት በጣም አስቸጋሪ |
| ከ18 እስከ 20 | ፕሮፌሽናል | ለመረዳት እጅግ በጣም አስቸጋሪ |

ከላይ በዝርዝር የተቀመጠውን የጉኒንግ ፎግ ኢንዴክስ ቀመርን በምሳሌ እንየው፡፡

አንድ ምንባብ በናሙናነት ቢወሰድና ምንባቡ 300 ቃላት፤ 25 አረፍተ ነገሮችና 7 ከሶስት በላይ ቀለማት ያሏቸው ከባድ ቃላት ቢኖሩት ምንባቡ ለየትኛው የክፍል ደረጃ ሊስማማ እንደሚችል ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

- የቃላት መጠን፦ 300
- የአረፍተ ነገር ብዛት፦ 25
- በምንባቡ ውስጥ የሚገኘው አማካይ የአረፍተ ነገር ርዝመት፦ 300/25 = 12
- የከባድ ቃላት መጠን፦ 7
- አማካይ የአረፍተ ነገር ርዝመት ሲደመር ከባድ የቃላት መጠን፦ 12 + 7 = 19
- 19 x 0.4 = 7.6

በተገኘው ውጤት መሰረት ይህ ምንባብ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎችን ሊመጥን የሚችል የተነባቢነት ደረጃ አለው ማለት ነው፡፡

## 2.7.የቀደምት ሀገርኛ ጥናቶች ቅኝት

አጥኚዋ ይህን ጥናት ስታካሂድ ከጥናቱ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን ሃገርኛ ጥናቶችን ለመዳሰስ ጥረት አድርጋለች፡፡ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ብዛት ያላቸው ጥናቶች ቀደም ብለው የተሰሩና አሁንም በመሰራት ላይ የሚገኙ ቢሆንም አጥኚዋ በአማርኛ ቋንቋ የተሰሩ ጥናቶችን በቻለችው መጠን ለመቃኘት ሞክራ ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ተዛማጅነት ያለው በፋንቱ ደምሴ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተጠና ጥናትና በግዛቸው በላይ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የተጠና ጥናታዊ ጽሁፍን ነው፡፡

በዚህም መሰረት በ1989 ዓ.ም. ፋንቱ ደምሴ የተባለች አጥኚ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህ ምረቃ ትምህርት ቤት “ የጾታ ልዩነት አማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድ ያለው ሚና በእንጦጦ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች አጠቃላይ የቋንቋ ብቃት” በሚል ርዕስ አማርኛን በማስተማር ስነ ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ባቀረበችው ጥናት በተጠቀሰው መቼትና የክፍል ደረጃ በሚገኙ ወንድና ሴት ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ ብቃት ረገድ የጾታ ልዩነት ያለውን ሚና ለመመርመር ሞክራለች፡፡

በተጨማሪም በ2007 ዓ/ም ግዛቸው በላይ የተባለው አጥኚ በባህርዳር ዩኒቨርሲትይ የድህረ- ምረቃ መርሃ-ግብር “የጾታ ልዩነት የአማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድ ያለው ሚና በአባይ ምንጭ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የቋንቋ ክሂል ችሎታ ላይ ያተኮረ ጥናት” በሚል ርእስ ያቀረበውን ጥናታዊ ጽሁፍ ለማቀኘት ሞክራለች፡፡

የፋንቱ ደምሴ እና የግዛቸው በላይ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስሉት ነገሮች በዋንኛነት የጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ፤ ጥናቱን በማካሄድ ሂደት የተከተለው ቅደም ተከተል፤ መረጃ የተሰበሰበበት ዘዴ እና የጥናቱ ውጤት የተተነተነበት መንገድ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል የፋንቱ ደምሴ እና የግዛቸው በላይ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚለያይበት ሁኔታ ደግሞ ጥናቱ የተጠናበት ጊዜ፤ ጥናቱ የተደረገበት ቦታ፤ ትምህርት ቤቱ እና በመረጃ ምንጭነት የተመረጡት ተማርዎች የክፍል ደረጃ በልዩነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## 3.የጥናቱ ዘዴና አካሄድ

ይህ ጥናት አማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድበወንድና ሴት ተማሪዎች መካከል ያለ ንጽጽር በዘጠነኛ ክፍል አፈ-ፈት ተማሪዎች ተተኳሪነት የሚለውን ርእሰ ጉዳይ መነሻ አድርጎ የነዚህን ተማሪዎቸ አጠቃላይ የቋንቋ ክሂል ችሎታ ለመለካት የግንዛቤ መለያ ሙከራና የቃል ፅህፈት ሙከራዎችን በመረጃ መሰብሰቢያነት በመጠቀም በመተንተንና በመተረጎም የሚደርስበትን የማጠቃለያ ሃሳብ ያቀርባል፡፡

### 3.1. የተጠኚዎች አመራረጥ

### 3.1.1. የትምህርት ቤት አመራረጥ

ለዚህ ጥናት የተመረጠው በኦሮሚያ ክልል በአርሲ ዞን በጮሌ ወረዳ ከሚገኙት አምስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በወረዳው ዋና ከተማ የሚገኘው ጮሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ አጥኚዋ ትምህርት ቤቱን ለመምረጥ መስፈርት ያደረገችው የይሁንኝ የናሙና አመራረጥ ስልት (Purposive Sampling) ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት አጥኚዋ በዚሁ ትምህርት ቤት የምታስተምር በመሆኑና ተጠኚዎቹም በዚሁ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች በመሆናቸው ጥናቱን በቅርበት ለማከናወንና ተጨባጭ መረጃ በወቅቱ ለመሰብሰብ አመቺ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

### 3.1.2. የተማሪዎች አመራረጥ

በይሁነኝ ናሙና (Purposive Sampling) በተመረጠው በጮሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ 2015 ዓ.ም. የትምህርት ዘመን በሚማሩ በ9ኛ ክፍል ወንድና ሴት ተማሪዎች ላይ ጥናቱ አተኩሯል፡፡ ጥናቱ የተካሄደበት የጮሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማርኛ አፈ-ፈትና ኢ-አፈ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች የሚማሩበት ትምህርት ቤት ነው፡፡ አማርኛ ኢ-አፈ ፈት የሆኑት ተማሪዎች አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የሚፈቱ ሲሆን አማርኛ ቋንቋን መማር የሚጀምሩት 5ኛ ክፍል ከደረሱ በኋላ ነው፡፡ ዘጠነኛ ክፍል ሲደርሱ ግን አፋቸውን በኦሮምኛ የፈቱትም ሆኑ አፋቸውን በአማርኛ የፈቱት ተማሪዎች በአንድ ክፍል ተደባልቀው ይማራሉ፡፡ አፋቸውን በኦሮምኛ የፈቱት ተማርዎች አማርኛ ቋንቋን ለአራት አመት ብቻ የተማሩ ሲሆን አፋቸውን በአማርኛ የፈቱት ግን ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ ቋንቋውን እየተማሩ ያሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም ከጥናቱ የሚገኘውን ውጤት ተጨባጭና አስተማማኝ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ጥናቱ አማርኛ አፈ-ፈት የሆኑ ተማሪዎችን ብቻ

በጥናቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ ተደርጓል። በተጨማሪም አጥኚዋ አፋቸውን በአማርኛ የፈቱ ተማሪዎችን ብቻ የመረጠችውም ክትምህርቱ ጋር ካላቸው ቀይታ አንጻር ነው።

በዚህም መሰረት በ2015 ዓ.ም. በዘጠነኛ ክፍል ትምህርታቸውን በ14 ክፍሎች በመከታተል ላይ ካሉ 302 ወንድ እና 351 ሴት በጥቅሉ 653 ተማሪዎች ውስጥ በተራ የዕጣናሙና አወሳሰድ ዘዴ (Simple Random Sampling method) 91 ወንድ እና 105 ሴት በጥቅሉ 196 አማርኛ አፈ-ፈት ተማሪዎች ተመርጠዋል። በናሙናነት የተመረጡት ተማሪዎች ቁጥር የአጠቃላዩን የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ቁጥር 30%ቱን ያህል ይወክላል። በጾታ አንጻር በኩልም ሲታይ ተመጣጣኝ የሆነ ውክልና ተሰጧቸዋል።

## 3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ይህንን ጥናት በማጥናት ሂደት ውስጥ የተጠኚ ተማሪዎችን አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ክሂል ችሎታ ልዩነትን ለመለካትበመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት የዋሉትየግንዛቤ መለያ ሙከራና የቃል ጽህፈት ናቸው።

### 3.2.1. የግንዛቤ ሙከራ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

የጾታ ልዩነት የአማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድ ያለውን ሚና በጮሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ጥናት ለማድረግ በዋነኛ መረጃ መሰብሰቢያነት አጥኚዋ በስራ ላይ ያዋለችው የግንዛቤ መለያ ሙከራ ነው።

የተማሪዎቹን የአማርኛ ቋንቋክሂል ብቃት ለመለካት የሚያስችሉ የግንዛቤ መለያ ሙከራዎችን ለማዘጋጀት ለተጠቀሰው የክፍል ደረጃ የሚመጥኑ ሶስት ምንባቦች ከተተለያዩ ምንጮች ተመርጠዋል። ከተመረጡት ሶስቱ ምንባቦች ውስጥ አንዱ ውድቅ ተደርጎ ሁለቱ የተመረጡ ሲሆን የተመረጡት ምንባቦች ለዘጠነኛ ክፍል ደረጃ የሚመጥኑ መሆናቸውን በፎግ ኢንዴክስ የተነባቢነት ቀመር መሰረት ተሰልቶና ተረጋግጦ ነው። ከሶስቱ ምንባቦች አንዱ ውድቅ የተደረገበት ምክንያት በፍግ ኢንዴክስ የተነባቢነት ቀመር መሰርት ሲሰላ ለዘጠነኛ ክፍል የማይመጥን በመሆኑና በተመረጡት የአማርኛ ቋንቋ ምምህራን እይታው ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ሊከብድ ይችላል በመባሉ ውድቅ ሊሆን ችሏል።

ከፎግ ኢንዴክስ ማረጋገጫ በተጨማሪ ምንባቦቹ በይዘታቸው ለአንድ ወገን ብቻ ቅርበት ወይም ዕውቅና ያላቸው እንዳይሆኑ ጥረት ተደርጓል። በዚህ ጉዳይ ላይ Savingo (1982) በግንዛቤ መለያ ሙከራ የሚመረጠው ምንባብ ከተወሰኑ አካላት ወይም ቡድኖች ቀደም ያለ ዕውቀት ጋር

የተቆራኘ እንዳይሆንና ያንድ ወገን ብቻ ተጠቃሚ እንዳያደርግ እንዲሁም የተለየ ዕውቀትን የሚጠይቁ ሙያ ነክ ቃላትን ያካተተ መሆን እንደሌለበት ታስረዳለች፡፡
በፎግ ኢንዴክስ ቀመር ስሌት አማካኝነት የተነባቢነት ክብደት ደረጃቸውተመዝነው የተመረጡት ምንባቦች በተመረጠው የክፍል ደረጃ ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች ሊከብዱ ወይም ሊቀሉስለሚችሉ ምንባቦችን በመምረጥ ረገድ የአማርኛ ቋንቋ ነባር መምህራን አስተያየት እንደተጨማሪ መመዘኛ ተወስዷል፡፡

በዚህም መሰረት ምንባቦቹ ከመመረጣቸው በፊት ጥናቱ በሚካሄድበት ትምህርት ቤት አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ 2 ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው ነባርና ረጅም የማስተማር አገልግሎት ያላቸው መምህራንን በማሳተፍ ስለአመራረጡ ግብዓት የሚሆን አስተያየትና ማሻሻያ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ የተሰጡትን የማስተካከያ ግብዓቶች መሰረት በማድረግ በምንባቦቹ ላይ ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል፡፡
አጥኚዋ ከላይ የተገለጹትን ምንባብ የመምረጥ ሂደቶችን በስራ ላይ በማዋል የመረጠቻቸው ሁለት ጽሁፎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የመጽሀፉ ርዕስ፦ ዮቶር (ኮብላይ ካህን)፤
   የመጽሀፉ ደራሲ፦ ዓለማየሁ ደመቀ
   የታተመበት ዓ.ም፡፡- 2013
   ምንባቡ የተወሰደበት የመጽሀፉ ክፍል፦ ገጽ 85-87
   የተወሰደው ምንባብ ቃላት ብዛት፦ 309
2. የመጽሀፉ ርዕስ፦ የተወጋ ልብ
   የደራሲው ስም፦ ትክክል ገና
   የታተመበት ዓ.ም፥- 2012
   ምንባቡ የተወሰደበት የመጽሀፉ ክፍል፦ ገጽ 91-92
   የተወሰደው ምንባብ ቃላት ብዛት፦ 347

ለተመዛኞቹ የቀረቡት ሁለቱም የግንዛቤ መለያ ሙከራዎች በ “ፎግኢንዴክስ” የተነባቢነት ቀመር መሠረት ተሰልተው በጥናቱ ለተመረጠው የክፍል ደረጃ ሊመጥኑ የሚችሉ መሆናቸው ታውቋል፡ ፡ የግንዛቤ መለያ ሙከራው አስተማማኝ የቋንቋ ክሂል ችሎታ መለኪያ ይሆን ዘንድ በምንባቡ ውስጥ የተገደፉት ቃላት መጠን ከአርባ እስከ ሃምሳ መሆን እንደሚኖርባቸው Heton (1990) በሚጠቅሰው መሰረት በተመረጡት ምንባቦች ውስጥ የተገደፉት ቃላት ብዛት (መጠን)አርባ አርባ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

ለሁለቱም የግንዛቤ መለያ ሙከራዎች የመልስ መስጫ ወረቀት ተዘጋጅቶ ተመዛኞች በመልስ መስጫ ወረቀቱ ላይ ለእያንዳንዱ የተገደፈ ቃል ምትክ ተስማሚ ነው ብለው የወሰኑትን ቃል እንዲያሰፍሩ ተደርጓል፡፡ በመልስ መስጫ ወረቀቱ ላይ በምንባቡ ውስጥ ከተገደፉት ቃላት እኩል የሆኑ ባዶ ቦታዎች ተቀምጠዋል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ተፈታኞች የክፍት ቦታዎችን መጠን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ቃሉ አጭር ወይም ረዥም ሊሆን ይችላል በሚል ግምት መልስ ለመስጠት የመሞከር አዝማሚያ እንዳይኖራቸው ለማድረግ ነው፡፡
ምዘናውን ተማሪዎቹ መስራት ከመጀመራቸው በፊት ከሙከራው ጋር አብሮ ተያይዞ ከቀረበው የፈተናውን ዝርዝር አካሄድና አሰራር የሚገልጸውን መመሪያ በሚገባ እንዲያነቡ ተደርጓል፡፡ ሁለቱ የግንዛቤ ሙከራዎች ለጥናቱ ለተመረጡት ተሳታፊዎች የቀረቡት በተለያየ ወቅት ነው፡፡ በተጨማሪም ሂደቱንና አሰራሩን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ የአሰራሩ መመሪያ በፈታኟ በኩል ለተፈታኞቹ በሚገባ ገለጻ ተደርጎላቸዋል፡፡
ለሁለቱም የግንዛቤ መለያ ሙከራዎችን ሰርቶ ለማጠናቀቅ ለእያንዳንዳቸው 40 ደቂቃ ተፈቅዷል፡፡ Oller (1979) እንደሚገልፀው ለእያንዳንዱ ጥያቄ አንድ ደቂቃ መስጠት ተገቢ ነው በማለት ይገልጻል፡፡ በመሆኑም አንዱን የግንዛቤ ሙከራ ለማጠናቀቅ የተፈቀደው ጊዜ አርባ ደቂቃ ነው፡፡ ተሳታፊዎቹ ሙከራውን በሚሰሩበት ጊዜም አጥኚዋና አንድ የአማርኛ ቋንቋ መምህር ተገኝተዋል፡፡ ግንዛቤ መለያ ሙከራዎችን ለማረምና ውጤት ለመስጠት ሁለት ዓይነት የአስተራረም ዘዴዎች እንዳሉ በተዛማጅ ጽሁፎች ክለሳ ስር በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ ለማስታወስም የተለመደው (ነባር) ቃል አስተራረም ዘዴና የተመሳሳይ ቃል አስተራረም ዘዴዎች ናቸው፡፡
የተለመደው ወይም የትክክለኛው ቃል አስተራረም ዘዴ ተመዛኙ ትክክለኛውን ወይም ዋናውን ቃል እንዲጠቀም የሚያደርግ ሲሆን በሌላ በኩል የተመሳሳይ ቃል አስተራረም ዘዴ ደግሞ ተመዛኙ ተቀባይነት ወይም ተገቢነት ያለው ተመሳሳይ ቃል እንዲጠቀም ያስችለዋል፡፡
በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ውስጥ አጥኚዋ ሙከራዎቹን ለማረም የመረጠችው የአስተራረም ዘዴ የተመሳሳይ ቃል የአስተራረም ዘዴ ነው፡፡የነባርን ወይም የተለመደውን የአስተራረም ዘዴን መጠቀም ለማረም ቀላልና ጊዜ የማይፈጅ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አንድ ቃል በሚገባበት ቦታ ተመሳሳይ ሃሳብ ሊሰጡ የሚችሉ ሌሎች ቃላት ሊኖሩ ስለሚችሉ ዋናው ጸሀፊ የተጠቀመውን ቃል ብቻ እንዲጽፍ ማድረጉ ለተፈታኙ አዳጋች ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በተፈታኙ ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡ በዚህ ምክንያት የተነሳ አጥኚዋ የተመሳሳይ ቃላት የአስተራረም ዘዴን ልትመርጥ ችላለች፡፡

የሁለቱም የግንዛቤ መለያ ሙከራ መልስ መስጫ ወረቀቶች በተማሪዎቹ ከተሞሉ በኋላ ተሰብስበው በጮሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንዲታረሙ ተደርጓል። ከዛ በፊት ግን ለአራሚ መምህራኑ ስለጥናቱ አላማና ስለአስተራረሙ ሂደት በአጥኚዋ ማብራሪያ ተሰጥቷል።

### 3.2.2. የቃል ጽህፈት

ጥናቱ የተነሳበትን ዋና ዓላማ ከግብ ለማድረስ በዚህ ጥናት ውስጥ የተጠኚዎቹን የቋንቋ ክሂል ችሎታ ለመለካት መረጃ ለመሰብሰብ አጥኚዋ ከተጠቀመችባቸው መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ውስጥ ሁለተኛው የቃል ጽህፈት ነው።

ምንባቦች ለአንድ ዓላማ ሲመረጡ የተነባቢነት ክብደት ደረጃቸው ሊተኮርባቸው ከታለመው አካላት አንጻርየሚመጥን እንዲሆን ያስፈልጋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ Savingo (1982) እንደምታስገነዝበው፤ በርካታ ዘይቤያዊ አነጋገሮች እንዲሁም መደበኛ ያልሆኑ እና ሙያ ነክ የሆኑ ቃላትን ያካተቱ ምንባቦች እንዳይመረጡና የምንባቦቹም ይዘት የተለየ ስልጠናን በሚጠይቅ ጉዳይ ላይ ያተኮረ እንዳይሆን ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ ገልጻለች።
በዚህ ጥናት ውስጥ ተመጣጣኝ የቃላት ብዛት ያላቸው በተለያዩ ሶስት ጸሀፍት የተጻፉ ሶስት ምንባቦች ተመርጠው በፎግ ኢንዴክስ የተነባቢነት የክብደት ደረጃ ቀመር መሰረት ተሰልተው ለ9ኛ ክፍል በሚመጥን የተነባቢነት ደረጃ ያላቸው ሁለቱ ምንባቦች ተቀንጭበው ተወስደዋል።

ለቃል ጽህፈት ሙከራ የተመረጡት ምንባቦች፤-

1. የመጽሀፉ ርዕስ፦ ዶክተር አሸብርና ሌሎችም

የደራሲው ስም፦ አሌክስ አብረሃም

የታተመበት ዓ.ም፦ 2012
ምንባቡ የተወሰደበት የመጽሀፉ ክፍል፦ ገጽ 103

2. የመጽሀፉ ርዕስ፦ ልጅነት
የደራሲው ስም፦ ዘነበ ወላ
የታተመበት ዓ.ም፦- 2000
ምንባቡ የተወሰደበት የመጽሀፉ ክፍል፦ ገጽ 31

የተመረጡት ምንባቦች ለቃል ፅህፈት አመቺ እንዲሆኑ በእያንዳንዱ ምንባብ ውስጥ የሚገኙ ቃላት በተወሰኑ ምድቦች ከተከፋፈሉ በኋላ ለጥናቱ ተሳታፊዎች የሚቀርቡበት ዓላማ ግልጽ ተደርጓል፡፡ በመቀጠልም እንዲገመግሙ ለተመረጡትሁለትልምድ ባላቸው የጮሌ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራንተሰጥተው የምንባቦቹን ይዘት፣ የሀሳብ አደረጃጀትና የቃላት አመራረጥ ከግምት በማስገባት፣ ለክፍሉ ደረጃ ይበልጥ ይመጥናሉ የሚሏቸውን በቅደም ተከተል በደረጃ እንዲያመላክቱ ተደርጐ ሶስቱም መምህራን የበለጠውን ነጥብ የሰጧቸው ሁለት ሙከራዎች ተመርጠዋል፤ በተጨማሪም መምህራኑ በምንባቦች አከፋፈል ረገድ የሰነዘሯቸውን ገንቢ አስተያየቶች መሰረት በማድረግ ተገቢው ማሻሻያ ታክሎበታል፡፡

ኦለር (1979) እንዲሁም Heton (1988) ከቃል ጽሁፍ ምንባቦች ጋር በተያያዘ እንደሚያስረዱት በቃል ፅሑፍ ምንባቦች ውስጥ የሚገኙትን ቃላት በየምድቡ በመከፋፈል ረገድ ተመራማሪዎች ተፈታኙ በአንድ አጭር የትውስታ ጊዜ (Short Term Memory Span) አዳምጦ እንዲጽፍ የሚነበቡለት ቃላት መጠን ከሰባት እስከ አስር መሆን እንዳለበት ነው፡፡ በሌላ በኩል Oller (1974) በአንዳንድ ሁኔታዎች የሚነበቡት ቃላት መጠን እስከ ሃያ ቃላት ሊደርስ ይችላል ይላሉ፡፡

ይህን ሃሳብ መነሻ በማድረግ በዚህ ጥናት ውስጥ ለጥናቱ ተሳታፊዎች በቀረቡት የቃል-ፅሑፎች ውስጥ በእያንዳንዱ ምድብ የሚገኙት ቃላት መጠን በአብዛኛው ከሰባት ያላነሱና ከአስራሁለት የማይበልጡ ናቸው፡፡

ሙከራው ከመጀመሩ በፊት ለተማሪዎቹ ስለሙከራው ሂደት ዝርዝር ማብራሪያ የተሰጠ ሲሆን ምንባቡ ሶስት ጊዜም እንደሚነበብላቸው ግልጽ ተደርጎላቸዋል፡፡

ከላይ በሠንጠረዥ ሁለት ስማቸው የተጠቀሰው መምህራን በዚህ ጥናታዊ ስራ ላይ ስማቸው እንዲገለፅ ፈቃደኝነታቸውን በአጥኚዋ ተጠይቀው ሁለቱም ፈቃደኛ በመሆናቸው ስማቸው ሊገለፅ ችሏል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4.የመረጃ አቀራረብና ትንተና

በዚህ ምዕራፍ ስር የጥናቱን ዋና ዓላማ መሰረት በማድረግ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በሙሉ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

### 4.1. የጥናቱ መረጃ ትንተና

የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ዋና አላማ በምዕራፍ አንድ ላይ እንደተገለፀው  አማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድ በወንድና ሴት ተማሪዎች መካከል ያለ ንጽጽር በጮሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የቋንቋ ክሂል ችሎታ ምን እንደሚመስል መመርመር ነው፡፡
ጥናቱ የተነሳበትን ዋና ዓላማ ከግብ ለማድረስ

- በዘጠነኛ ክፍል ሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክሂል ብቃት ችሎታ ተጨባጭ ልዩነት አለ ወይስ የለም?
- የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ክሂልን ከመማር አንጻር የጾታ ልዩነት ያለው አንድምታ ምንድነው?

በማለት የተነሱትን ጥያቄዎች በጥልቀትመርምሮ ምላሽ ለማግኘት ይቻል ዘንድ በተጠኚ ተማሪዎች የቃል ጽህፈትና የግንዛቤ ሙከራ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ የተጠኚዎቹን የቋንቋ ክሂል ችሎታ በጥናቱ የተደረሰበትን ውጤት መተንተን ነው፡፡

91 ወንድና 105 ሴት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን (በጥቅሉ 196 ተማሪዎች) በናሙናነት ያሳተፈው ይህ ጥናት በግንዛቤ ሙከራ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችና የቃል ጽህፈት ሙከራዎች በሁለቱም ጾታዎች የተመዘገበው ውጤት በዚህ ጥናት መጨረሻ በአባሪ ክፍል ተያይዟል፡፡

ሁለቱም የግንዛቤ መለያ ሙከራዎች እያንዳንዳቸው አርባ አርባ የተገደፉ ቃላት አሏቸው፡፡ በድምሩ 80 የተገደፉ ቃላት አሏቸው፡፡ውጤቱ ሲታረምም ከ80%ሆኖ ከቃል ጽህፈት ጋር ያላቸውን ተዛምዶና ንጽጽር በአቻነት ለማስላት ይቻል ዘንድ ከ80% የነበረው ውጤት ወደ 100% ተቀይሯል፡፡ በዚህም መሰረት በግንዛቤ መለያ ሙከራዎች ከወንድ ተጠኚዎች ከፍተኛው ውጤት87%ሲሆን ዝቅተኛው ውጤት ደግሞ34% ነው፡፡

በቃል ጽህፈት ሙከራ ደግሞ ወንድ ተጠኚዎች ያስመዘገቡት ከፍተኛው ውጤት 95.5% ሲሆን ዝቅተኛው ውጤት ደግሞ 42.5% ነው፡፡

በሌላ በኩልበሴት ተጠኚዎች በግንዛቤ መለያ ሙከራ የተመዘገበ ከፍተኛው ውጤት 82% ሲሆን 34% ደግሞ ዝቅተኛ ውጤት ሆኖ በሴቶች ተመዝግቧል፡፡ በቃል ጽህፈት ሙከራ ውጤት 88.5% በሴቶች የተመዘገበ ከፍተኛው ውጤት ሲሆን 35% ደግሞ ዝቅተኛ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡

በአጠቃላይ በጥናቱ የተገኘውን ውጤት ጥናቱ ሲጀምር ካነሳቸው መሰረታዊዓላማናጥያቄዎች አንጻር ከዚህ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ተደግፎ ይቀርባል፡፡

**ሰንጠረዥ 2፡ በግንዛቤ መለያ ሙከራ ወንድ ተጠኚ ተማሪዎች ያስመዘገቡት ውጤት**

| የሙከራው ዓይነት | ብዛት | M | Sd |
|---|---|---|---|
| የግንዛቤ መለያ ሙከራ | 91 | 53.26 | 10.19 |

ከላይ ከፍ ብሎ በሰንጠረዥ 3 ለማሳየት እንደተሞከረው53.26% ወንድ ተማሪዎች በግንዛቤ መለያ ሙከራ ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት ነው፡፡ በስሌቱ መሰረት የወንድ ተማሪዎች የግንዛቤ መለያ ሙከራ ስታንዳርድ ዲቪዬሽን 10.19ነው፡፡ይህ ውጤት የሚያሳየው በግንዛቤ መለያ ሙከራ አብዛኞቹ ወንድ ተማሪዎች ከማለፊያው ውጤት በላይ ነው ያገኙት፡፡

**ሰንጠረዥ 3፡ በቃል ጽህፈት ሙከራ ወንድ ተጠኚ ተማሪዎች ያስመዘገቡት ውጤት**

| የሙከራው ዓይነት | ብዛት | M | Sd |
|---|---|---|---|
| የቃል ጽህፈት ሙከራ | 91 | 64.66 | 11.45 |

ከፍ ብሎ በሰንጠረዥ 4 ለማሳየት እንደተሞከረው ለወንድ ተጠኚ ተማሪዎች ከተሰጠው የቃል ጽህፈት ሙከራ የተሰላው አማካይ ውጤት 64.66ሲሆን ባስመዘገቡት ውጤት የተገኘው ስታንዳርድ ዲቪዬሽን ደግሞ 11.45ነው፡፡ ከዚህ ትንተና መረዳት የሚቻለው እንደ ግንዛቤ መለያ ሙከራ ሁሉ አብዛኞቹ ወንድ ተጠኚ ተማሪዎች በሙከራው ያገኙት ውጤት ከማለፊያው ነጥብ በላይ ነው፡፡

**ሰንጠረዥ 4፡ በግንዛቤ መለያና በቃል ጽህፈት ሙከራ ወንድ ተጠኚ ተማሪዎች ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት (M) እና ስታንዳርድ ዲቪየሽን (Sd) ንጽጽርና በሁለቱ መካከል ያለው ተዛምዶ**

| የሙከራው ዓይነት | ብዛት | M | Sd | ተዛምዶ(r) | የተዛምዶው ዓይነት |
|---|---|---|---|---|---|
| የግንዛቤ መለያ ሙከራ | 91 | 53.26 | 10.19 | 0.4201 | አዎንታዊ መካከለኛ |
| የቃል ጽህፈት ሙከራ | 91 | 64.66 | 11.45 | | |

**በሰንጠረዥ 4** እንደተመለከተው ወንድ ተማሪዎች በቃል ጽህፈት ሙከራ ያገኙት አማካይ ውጤት 64.66እና ስታንዳርድ ዲቪየሽን 11.45በግንዛቤ መለያ ሙከራ ካገኙት አማካይ ውጤት 53.26እና10.19 ስታንዳርድ ዲቪዬሽን በልጦ ተገኝቷል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የተገኘው ውጤት በንጽጽር ልዩነቱ ሲታይ በመካከላቸው ያለው ስታንዳርድ ዲቪዬሽን 0.26 ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው ተማሪዎቹ በሁለቱ ሙከራ ያገኙት አማካይ ውጤት ልዩነት ቢኖረውም በስርጭት አኳያ የጎላ ልዩነት እንደሌላቸው ነው፡፡ በሌላ በኩልተሰልቶ የተገኘው በሁለቱ ሙከራዎች ውጤት መካከል ያለው ተዛምዶ (Correlation coefficient)0.4201 ነው፡፡

ኢቫንስ (1996) የሁለት ቫሪያብልስ ተዛምዶ ወይም ግንኙነት ከ -1 እስከ +1 ድረስ ሊቀመጥ የሚችል ሲሆን ከዜሮ በታች (<0) እስከ ኔጌቲቭ 1 (-1) ድረስ ያለው አሉታዊ (Negative) ግንኙነት ከ ዜሮ በላይ (>0) እስከ 1 (+1)ያለው ደግሞ አዎንታዊ (Positive) ግንኙነት አላቸው በማለት ያስረዳል፡፡ በግልጽ ለማየት የግንኙነቱን ወይም የተዛምዶውን ውጤትከዚህ እንደሚከተለው ማየት ይቻላል፡፡

- 0.00-0.19 - በጣም ደካማ
- 0.2-0.39 - ደካማ
- 0.4-0.59 - መካከለኛ

- 0.6 — 0.79 ጠንካራ
- 0.8 — 1.0 በጣም ጠንካራ ነው

በዚህም መሰረት በወንድ በሰንጠረዥ 5 እንደተመለከተው በሁለቱ ሙከራዎች መካከል ያለው የግንኙነት ውጤት (Correlation coefficient)0.4201በመሆኑ በውጤቶቹ መካከል አዎንታዊ የሆነ መካከለኛተዛምዶ እንዳለ ለመረዳት ያስችላል።

**ሰንጠረዥ 5**፡ በግንዛቤ መለያ ሙከራ ሴት ተጠኚ ተማሪዎች ያስመዘገቡት ውጤት

| የሙከራው ዓይነት | ብዛት | M | Sd |
|---|---|---|---|
| የግንዛቤ መለያ ሙከራ | 105 | 54.52 | 10.46 |

በግንዛቤ መለያ ሙከራ ሴት ተጠኚ ተማሪዎች ያስመዘገቡት ውጤት በሰንጠረዥ 6 እንደሚታየው 54.52አማካይ ውጤታቸውሲሆን10.46ደግሞ ስታንዳርድ ዲቪዬሽን ነው።ሴት ተማሪዎችም እንደ ወንድ አቻዎቻቸው ሁሉ በዚህ ሙከራ አማካይ ውጤታቸው ከማለፊያው ነጥብ የዘለለ ነው።

**ሰንጠረዥ 6**፡ በቃል ጽህፈት ሙከራ ሴት ተጠኚ ተማሪዎች ያስመዘገቡት ውጤት

| የሙከራው ዓይነት | ብዛት | M | Sd |
|---|---|---|---|
| የቃል ጽህፈት ሙከራ | 105 | 67.9 | 10.96 |

**ሰንጠረዥ 7**: በሴት ተማሪዎች የተመዘገበውን የቃል ጽህፈት ሙከራ ውጤት ያሳያል። በዚህም መሰረት የሴት ተማሪዎች አማካይ ውጤትና ስታንዳርድ ዲቪዬሽን በቅደም ተከተል 67.9እና10.96ሆኖ ተመዝግቧል።

**ሰንጠረዥ 8**፡ በግንዛቤ መለያና በቃል ጽህፈት ሙከራ ሴት ተጠኚ ተማሪዎች ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት (M) እና ስታንዳርድ ዲቪየሽን (Sd) ንጽጽርና በሁለቱ መካከል ያለው ተዛምዶ

| የሙከራው ዓይነት | ብዛት | M | Sd | ተዛምዶ(r) | የተዛምዶው ዓይነት |
|---|---|---|---|---|---|
| የግንዛቤ መለያ ሙከራ | 105 | 54.45 | 10.74 | 0.4578 | አዎንታዊ መካከለኛ |
| የቃል ጽህፈት ሙከራ | 105 | 67.9 | 10.96 | | |

ሰንጠረዥ ስምንት በግንዛቤ መለያና በቃል ጽህፈት ሙከራ ሴት ተጠኚ ተማሪዎች ያስመዘገቡት አማካይውጤት (M) እና ስታንዳርድ ዲቪየሽን (Sd) ንጽጽርና በሁለቱ መካከል ያለው ተዛምዶን (r) ያመለክታል፡፡ እንደ ሰንጠረዥ ስምንት ከሆነ የሁለቱ ሙከራዎች የሴት ተማሪዎች አማካይ ውጤት ከግንዛቤ የሚገባ ልዩነት ያለው ሲሆን በቃል ጽህፈት የተመዘገበው ውጤት ከግንዛቤ መለያ ሙከራ ውጤት አንጻር የተሻለ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ምክኒያቱም በቃል ጽህፈት ሙከራ ውጤትና በግንዛቤ መለያ ሙከራ ውጤት የተመዘገበው ስታንዳርድ ዲቪዬሽን በቅደም ተከተል 10.96 እና 10.74 ነው፡፡ከዚህ መረዳት የሚቻለው በሁለቱ ሙከራ ውጤቶች መካከል ያለው የስታንዳርድ ዲቪዬሽን ወይም ስርጭት ልዩነት 0.22ብቻ መሆኑን ነው፡፡

በሁለቱ ሙከራ ውጤቶች መካከል ሊኖር የሚችለውን ተዛምዶ(Correlation coefficient) ለማነጻጸር በተደረገው ስሌት ሴት ተጠኚ ተማሪዎች ባስመዘገቡት የግንዛቤ መለያ ሙከራና የቃል ጽህፈት ሙከራ ውጤት መካከል 0.4578 የሆነ አዎንታዊ መካከለኛ ግንኙነት መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

**ሰንጠረዥ 9፡ አጠቃላይ ወንድና ሴት ተማሪዎች በግንዛቤ መለያ ሙከራያገኙት ውጤት ንጽጽር**

| ጾታ | ብዛት | M | SD | Df | t | P value |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ወንድ | 91 | 52.63 | 10.07 | 194 | 0.8509 | 0.3959 |
| ሴት | 105 | 54.45 | 10.74 | | | |

መግለጫ፦ df- degrees of freedom; t- t-test;

P value- likelihood that an observed outcome is the result of chance.

ከፍ ብሎ በሰንጠረዥ 9 ተጠኚ ወንድና ሴት ተማሪዎች በግንዛቤ መለያ ሙከራ ያገኙት ውጤት በንጽጽር ቀርቧል:: በዚህም መሰረት ሁለቱ ተጠኚ ጾታዎች በግንዛቤ መለያ ሙከራ ያገኙት አማካይ ውጤትና ስታንዳርድ ዲቪዬሽን የተወሰነ ልዩነት ያሳያል::ይሁን እንጂ በሁለቱ ጾታዎች ውጤትመካከል ተጨባጭ የሆነ ልዩነት መኖር አለመኖሩን በትክክል ለማሳየት በቲ ቴስት (t-test) ቀመር የተሰላው ውጤት (t) ከላይ በሰንጠረዥ 9 ተቀምጧል::

ቲ ቴስት (t-test)የሁለት ምድብ ተጠኚዎች አማካይ ውጤትን ለማወዳደር የሚያገለግል ስታትስቲካል ሙከራ ነው:: ቲ ቴስት በስታትስቲክስ ውስጥ መላምታዊ ሙከራን ለማድረግ ያገለግላል:: በዚህም መሰረት ተሰልቶ የተገኘው የቲ ቴስት ውጤት 0.8509 ሲሆን በሁለቱ ጾታዎች መካከል በግንዛቤ መለያ ሙከራ በነበረው 194 የልውውጥ ነጻነት(df)እንዲሁም በ95% የተቀባይነት ወይም እርግጠኛነት ስሌትአስተማማኝ መሆን ከሚጠበቀው 1.9723 ያነሰ ነው:: በመሆኑም የልዩነቱ ደረጃ የማያስተማምን ወይም ከግምት የሚገባ አይደለም:: ምክኒያቱም በቲ ቴስት የተገኘው ውጤትልዩነት መኖሩን በአስተማማኝ ሊያሳይ ከሚችለው መስፈርት መለኪያ አንጻር ያነሰ ሆኖ በመገኘቱ ነው::

**ሰንጠረዥ 10፡ አጠቃላይ ወንድና ሴት ተማሪዎች በቃል ጽህፈት ሙከራ ያገኙት ውጤት ንጽጽር**

| ጾታ | ብዛት | M | SD | Df | to | P value |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ወንድ | 91 | 64.68 | 11.45 | 194 | 1.8505 | 0.0658 |
| ሴት | 105 | 67.9 | 10.96 | | | |

መግለጫ፦ df- degrees of freedom;

t-t-test

P value- likelihood that an observeoutcome is the result of chance.

ከሰንጠረዥ 10 መረዳት እንደሚቻለውወንድና ሴት ተጠኚ ተማሪዎች በቃል ጽህፈት ሙከራ ያገኙት ውጤት ተጠቃሎ ከተሰላ በኋላ የተገኘው የቲ ቴስት (t) ዋጋ 1.8505 ነው:: በስታስቲካል ስሌቱ መሰረት ይህ ውጤት በሁለቱ ጾታዎች መካከል በቃል ጽህፈት መለያ ሙከራ በነበረው 194 የልውውጥ ነጻነት(df) እንዲሁም በ95% የተቀባይነት ወይም እርግጠኛነት ስሌት አስተማማኝ መሆን ከሚጠበቀው 1.9723 ያነሰ ነው:: በመሆኑም የልዩነቱ ደረጃ የማያስተማምን

ወይም ከግምት የሚገባ አይደለም፡፡ ምክኒያቱም በቲ ቴስት የተገኘው ውጤት ልዩነት መኖሩን በአስተማማኝ ሊያሳይ ከሚችለው መስፈርት መለኪያ አንጻር ያነሰ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

**ሰንጠረዥ 11፡ በሁለቱ ሙከራዎች በሁለቱም ጾታዎች የተገኘው ውጤት ንጽጽር**

| ብዛት | የሙከራው ዓይነት | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የግንዛቤ መለያ | | የቃልጽህፈት | |
| | M | SD | M | SD |
| 196 | 53.89 | 10.35 | 67.24 | 11.31 |

ከላይ ከፍ ብሎ በሰንጠረዥ 11 እንደተመለከተው በዚህ ጥናት ውስጥ በተጠኚነት የተመረጡት በጥቅሉ 196 (91 ወንድ እና 105 ሴት) ተማሪዎች ሲሆኑየግንዛቤ መለያ ሙከራ ወስደው ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት 53.89 ሲሆን ስታንዳርድ ዲቪዬሽን ደግሞ 10.35 ነው፡፡ በሌላ በኩል የቃል ጽህፈት ሙከራ ወስደው ያገኙት አማካይ ውጤት 67.24 ሲሆን ስታንዳርድ ዲቪዬሽኑ ደግሞ 11.31 ነው፡፡ ከቀረበው ውጤት ማየት እንደሚቻለው በቃል ጽህፈት ተጠኚ ተማሪዎቹ ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት በግንዛቤ መለያ ሙከራ ካስመዘገቡት ውጤት ብልጫ እንዳለው ነው፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአማካይ የተመዘገበው ስታንዳርድ ዲቪዬሽን ውጤት የሚያሳየው በአጠቃላይ ተጠኚ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ክሂል ችሎታ መካከል የሰፋ ልዩነት አለመኖሩን ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ በውጤታቸው መካከል በጣም የናረ ወይም በጣም የወረደ ውጤት የለም፡፡ በጥቅሉ ተጠኚ ተማሪዎቹ ያላቸው ወቅታዊ አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ ተመጣጣኝ የሚባል ዓይነት ነው፡፡

ከላይ በዝርዝር ከቀረበው ትንታኔ በመነሳትበቀጣዩ ክፍል በጥናቱ ለተነሱት መሰረታዊ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል፡፡

## 4.2. የውጤት ማብራሪያ ከጥናቱ ዓላማና መሰረታዊ ጥያቄዎች አንጻር

- **ጥያቄ አንድ፦ በዘጠነኛ ክፍል ሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክሂል ብቃት ችሎታ ተጨባጭ ልዩነት አለ ወይስ የለም?**

ቀደም ባለው ክፍል ከቀረቡት ሰንጠረዦች ትንታኔ እንዳስተዋልነው በወንድና ሴት ተጠኚ ተማሪዎች መካከል ያለውን አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ክሂል ችሎታ ልዩነትን ለመፈተሽ በተሰጡት ሙከራዎች በቃል ጽህፈት ሙከራ የተመዘገበው ውጤት በግንዛቤ መለያ ሙከራ ከተመዘገበው ውጤት የተሻለ ነው። ይህም ልዩነት የተመዘገበው በሁለቱም ጾታዎች ነው። በግንዛቤ መለያ ሙከራ የወንድ ተጠኚ ተማሪዎችና የሴት ተጠኚ ተማሪዎች ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት በቅደም ተከተል 53.26 እና 54.52 ነው። ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው በግንዛቤ መለያ ሙከራ ሴት ተማሪዎች ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት ከወንድ አቻዎቻቸው በ1.26 የሚበልጥ ነው።

በሌላ በኩል እንደ ግንዛቤ መለያ ሙከራ ሁሉ በቃል ጽህፈት ሙከራ በሁለቱ ጾታዎች መካከል የተወሰነ የአማካይ ውጤት ልዩነት አለ። ወንድ ተጠኚ ተማሪዎች 64.66 ሴት ተጠኚ ተማሪዎች ደግሞ 67.819 አስመዝግበዋል። የሴት ተጠኚ ተማሪዎች አማካይ ውጤት ከወንድ አቻዎቻቸው በ 3.16 ይልቃል።

የአጠቃላይ ተጠኚ ተማሪዎችን (196 ተማሪዎች) አማካይ ውጤት ስንቃኝ ደግሞ በግንዛቤ መለያ ሙከራ ያስመዘገቡት ውጤት 53.86 ሲሆን በቃል ጽህፈት ሙከራ ደግሞ የተመዘገበው አማካይ ውጤት ደግሞ 67.24 ነው። ይህ የሚያሳየው በሁለቱ ሙከራዎች ተጠኚ ተማሪዎቹ ያስመዘገቡት ውጤት የሰፋ ልዩነት እንዳለው ነው። የዚህ ጥናት አቅራቢ በሁለቱ ሙከራዎች መካከል ለተመዘገበው የውጤት ልዩነት ምክኒያት የሆኑትን ነገሮች ለመመርመር በቀጣይ በዚህ ርዕስ ዙሪያ ሌላ ጥናት መደረግ አለበት ብላ ታምናለች።

በሁለቱ ሙከራዎችና በሁለቱ ጾታዎች መካከል የተመዘገበውን የአማካይ ውጤት ልዩነት በትክክል ከግንዛቤ የሚገባ የማይገባ መሆኑን ለማረጋገጥ ጥናቱ በቲ ቴስት (t-test) አማካኝነትተሰልቷል።በዚህም መሰረት ተሰልቶ የተገኘው የቲ ቴስት ውጤት 0.8509 ሲሆን በሁለቱ ጾታዎች መካከል በግንዛቤ መለያ ሙከራ በነበረው 194 የልውውጥ ነጻነት(df) እንዲሁም በ95% የተቀባይነት ወይም እርግጠኛነት ስሌት አስተማማኝ መሆን ከሚጠበቀው 1.9723 ያነሰ ነው። በመሆኑም የልዩነቱ ደረጃ የማያስተማምን ወይም ከግንዛቤ የሚገባ አይደለም።

ይህ የጥናት ግኝት ከግንዛቤ መለያ ሙከራ አንጻር ከዚህ ቀደም በፋንቱ ደምሴ (1989 ዓ.ም.) ከተጠናው ጥናት ውጤት ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን ፋንቱ በጥናቷ ግኝት እንዳረጋገጠችው ለጥናት በተመረጡት የ11ኛ ክፍል ወንድና ሴት ተማሪዎች መካከል በግንዛቤ መለያ ሙከራ አማካይ ውጤት ከግምት የሚገባ ልዩነት እንደሌለ ነው።

በተመሳሳይ ሁኔታ በዚህ ጥናት በቲ ቴስት (t-test) ስሌት ለማረጋገጥ እንደተቻለውወንድና ሴት ተጠኚ ተማሪዎች በቃል ጽህፈት ሙከራ ያገኙት ውጤት ተጠቃሎ ከተሰላ በኋላ የተገኘው የቲ ቴስት (t) ዋጋ 1.8505 ነው። ይህም የተቀባይነት ወይም እርግጠኛነት ስሌት አስተማማኝ መሆን ከሚጠበቀው 1.9723 ያነሰ ነው። በመሆኑም የልዩነቱ ደረጃ የማያስተማምን ወይም ከግምት የሚገባ አይደለም። ምክኒያቱም በቲ ቴስት የተገኘው ውጤት ልዩነት መኖሩን በአስተማማኝ ሊያሳይ ከሚችለው መስፈርት መለኪያ አንጻር ያነሰ ሆኖ በመገኘቱ ነው።

በቃል ጽህፈት ሙከራ ረገድ በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት በ1989 ዓ.ም. በዚሁ የጥናት ርዕስ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ በፋንቱ ደምሴ አማካኝነት ከተሰራው ጥናት ግኝት ጋር ተመሳሳይነት የለውም። ፋንቱ በጥናቷማጠቃለያ ለማሳየት እንደሞከረችው በቃል ጽህፈት ሙከራ ተሰልቶ የተገኘው የ ቲ ቴስት ዋጋ ለልዩነቱ አስተማማኝ መሆን ከሚጠበቀው ዋጋ በልጦ በመገኘቱ ሴት ተጠኚ ተማሪዎች ከወንድ ተጠኚ ተማሪዎች የተሻሉ እንደሆኑ ገልጻለች። ይሁን እንጂ የጠቅላላ ተጠኚዎቹ ውጤት ልዩነት አስተማማኝ መሆን ከሚጠበቀው ዋጋ ያነሰ በመሆኑ ልዩነቱ ከግምት የሚገባ እንዳልሆነ ጨምራ ገልጻለች።

በዚህም መሰረት የዚህ ጥናት ውጤት እናዳረጋገጠው በዘጠነኛ ክፍል ሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክሂል ብቃት ችሎታ ከግንዛቤ አለያም ከግምት የሚገባ ተጨባጭ ልዩነት እንደሌለ ነው። በዚህ ጥናት ምዕራፍ አንድ ስር በዝርዝር ለማየት እንደተሞከረው በወንድና ሴት ተማሪዎች መካከል ስላለው የቋንቋ ችሎታ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ አጥኚዎች ተጠንተው ከተገኙ በዛ ካሉ የጥናት ግኝቶች አንጻር ይህ ጥናት ተመሳሳይነት የለውም።ለምሳሌ ዊሊያምስ (1985) በጥናት ግኝቷ እንደገለጸችው በማናቸውም የዕድሜ ደረጃ ሴት ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት፣ በቃላት እውቀት መጠን በንባብ ክሂል ወዘተ … ከወንዶች የተሻሉ መሆናቸውን ስትገልጽ ኦልሰን (1979) ደግሞ በንባብ ክሂል ረገድ በየትኛውም የዕድሜ ክልልላይ የሚገኙ ሴቶች ከወንዶች የተሻሉ ሆነው መገኘታቸውን ይጠቁማል።

ይሁን እንጂ ቤትዝና ፊትዝጀራልድ (1987) እንዲሁም ዋሪክና ናግሊየር (1989) የጥናት ውጤት ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡

- **ጥያቄ ሁለት፦ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ክሂልን ከመማር አንጻር የጾታ ልዩነት ያለው አንድምታ ምንድነው?**

ሌላው ይህ ጥናት ካነሳቸው ጥያቄዎች ውስጥ ሁለተኛው የአማርኛ ቋንቋ ክሂልን ከመማር አንጻር ሴት ወይም ወንድ መሆን ያለውን አንድምታ ምን እንደሆነ መፈተሽ ነበረ፡፡ የዚህ ጥናት ውጤት እንዳረጋገጠው በራሱ ሴት ወይም ወንድ መሆን የአማርኛ ቋንቋ ክሂልን ከመማር ረገድ ከትርጉም ወይም ከግንዛቤ የሚገባ ልዩነት እንደሌለው ነው፡፡ይሁን እንጂ በተወሰነ መልኩ ሴት ተማሪዎች ከወንድ አቻዎቻቸው አንጻር የተሻለ የቋንቋ ችሎታ እንዳላቸው የዚህ ጥናት ውጤት ያሳያል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ዴቦራ ካሜሩን (1985) ባቀረበችው ጥናት የጾታ ልዩነት የቋንቋ ክሂልን ከመማር አንጻር ጎልቶየሚታይ በቂ ማረጋገጫ አለመኖሩን ጠቁማለች፡፡

በሌላ በኩል የአንዳንድ ጥናቶች ግኝቶች እንደሚያመለክቱት በቋንቋ መልመድ ረገድ ሴቶች ከወንዶች የተሻሉ መሆናቸውን ነው፡፡ ቤትዝና ፊትዝጀራልድ (1987) ሴት ልጆች ከወንድ ልጆች ቀድመው አፋቸውን እንደሚፈቱ ሲጠቁሙ ዊሊያምስ (1985) ደግሞ በቋንቋ መማር (መልመድ) ረገድ ሴት ከወንድ በእጅጉ ትፈጥናለች ብለው ይተነትናሉ፡፡

በተጨማሪም እነዚህ ተመራማሪዎች ሴቶች የተሻለ የቋንቋ ችሎታ ሊኖራቸው የቻለው ምናልባት ሴቶች ከወንዶች የበለጠ ተናጋሪ ናቸው ከሚለው አመለካከት በመነሳት ወላጆች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ከወንዶች ልጆቻቸው ይልቅ ከሴቶች ልጆቻቸው ጋር መነጋገር ስለሚያዘወትሩና፣ ይህም በበኩሉ የሴት ህፃናትን የቋንቋ ችሎታ በማዳበር ረገድ አስተዋጽኦ ሊያደርግ በመቻሉ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል የሚዘግቡ ጥናቶች መኖራቸውን ይገልፃሉ፡፡

በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ግኝት የሚያመለክተው የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ክሂልን ከመማር አንጻር የጾታ ልዩነት ያለው አንድምታይህን ያህል ከግንዛቤ የሚገባ እንዳልሆነ ነው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5. ማጠቃለያና አስተያየት

### 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ አማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድ በወንድና ሴት ተማሪዎች መካከል ያለ ንጽጽር በጮሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የቋንቋ ክሂል ችሎታ ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው::በዚህ መሰረት በጥናቱ ሊመለሱ የሚገባቸው ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎች ተጠቅሰዋል፡፡ እነሱም

- በዘጠነኛ ክፍል ሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክሂል ብቃት ችሎታ ተጨባጭ ልዩነት አለ ወይስ የለም?
- የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ክሂልን ከመማር አንጻር የጾታ ልዩነት ያለው አንድምታ ምንድነው?

የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ጥናቱ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት አርሲ ዞን ጮሌ ወረዳ በሚገኘው የጮሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ የተደረገ ሲሆን ትኩረቱንም ያደረገው በ2015 ዓ.ም. 9ኛ ክፍል ከሚማሩ ተማሪዎች ውስጥ በተራ የዕጣናሙና አወሳሰድ ዘዴ በተመረጡ 91 ወንድና 105 ሴት ተማሪዎች ላይ ነው::

በጥናቱ ለተነሱት ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት እና የተጠኚ ተማሪዎችን አጠቃላይ የቋንቋ ክሂል ብቃትን ለመለካት የግንዛቤ መለያ ሙከራ እና የቃል ጽህፈትየመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በመሆን አገልግለዋል። ይህም የሆነበት ምክኒያት በምዕራፍ ሁለት በስፋት በተለያዩ የዘርፉ ምሁራን እንደተገለጸው የቋንቋ አጠቃላይ ብቃትን ለመለካት ተገቢና አስተማማኝ መመዘኛዎች በመሆናቸው ነው። በተጨማሪም እነኚህ ሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ ሙሳሪያዎች ከጾታ ጋር ተያይዞ የቋንቋ ክሂልን ለመመዘን የሚያስችሉ የተሻሉ መለኪያዎች መሆናቸውን በቁጥር አናሳ የማይባሉ ጥናቶች ያስረግጣሉ።

ሙከራዎቹ ከዝግጅታቸው አንስቶ እስከ እርማታቸው ድረስ ጥንቃቄ ተደርጎባቸው ለተጠኚ ተማሪዎች እንዲቀርቡ ተደርጓል።ለምዘናው ተስማሚ ናቸው ተብለው የተገመቱ ምንባቦች ከተመረጡ በኋላ በፎግ ኢንዴክስ የተነባቢነት ቀመር መሰረት ተሰልተው ለ9ኛ ክፍል ደረጃ መመጠናቸው የተረጋገጠ ሁለት የግንዛቤ መለያ ሙከራና ሁለት የቃል ጽህፈት ምንባቦች በጥናቱ ላይ ውለዋል። በፎግ ኢንዴክስ ስሌት መሰረት የተመረጡት የግንዛቤ መለያ ሙከራ አንድ ዋጋ 9.156 ሲሆን የሙከራ ሁለት ዋጋ ደግሞ 9.63 መሆኑ ተረጋግጧል። በሌላ በኩል በቃል ጽህፈት

ሙከራ የተመረጡት የሙከራ አንድ እና ሁለት ስሌት በቅደም ተከተል 9.04 እና 9.76 ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም አማርኛን በማስተማር ረጅም ልምድ ያላቸውና አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው ሁለት መምህራንን በማሳተፍ የተመረጡት ምንባቦችን ይዘት፣ የቃላት አጠቃቀምና የሀሳብ አደረጃጀትን ገምግመው እንዲመርጡና የማስተካከያ ግብዓት እንዲሰጡ ተደርጎበመቀጠልም በተሰጠው ግብዓት መሰረት የተወሰኑ ማሻሻያዎች ምንባቦቹ ላይ ተደርጎባቸው ለጥናቱ ብቁ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

ከላይ በተጠቀሰው ሂደት የተመረጡት የግንዛቤና የቃል ጽህፈት ሙከራዎች በተለያየ ጊዜ ለተማሪዎቹ ቀርበው የመልስ ወረቀቶቹ ከተሰበሰቡ በኋላ በሁለት አራሚዎች እንዲታረሙ ተደርጓል፡፡በምዕራፍ ሶስት ክፍል 3.2.1 በተጠቀሰው መሰረት አራሚዎቹ የተመሳሳይ ቃል አስተራረም ዘዴን በመጠቀም የግንዛቤ መለያ ሙከራዎችን ዋናውን ምንባብ በማመሳከር ደግሞ የቃል ጽህፈቶቹን አርመዋል፡፡መምህራኑ ያረሙትን ደምረው የእያንዳንዱን ተማሪ ውጤት ከመቶ (100%) አስፍረዋል፡፡

አጠቃላይ ተጠኚ ተማሪዎቹ በግንዛቤ መለያ ሙከራ ያስመዘገቡት ውጤት ተሰልቶ የተገኘው አማካይ ውጤት 53.89 ሲሆን በቃል ጽህፈት ያገኙት አማካይ ውጤት ደግሞ 67.24 ነው፡፡ ከአጠቃላይ ውጤታቸው ለመረዳት እንደሚቻለው በቃል ጽህፈት የተመዘገበው ውጤት ከግንዛቤ መለያ ሙከራ አንጻር የተሻለ መሆኑን ነው፡፡ ለዚህ ልዩነት ምክኒያት ሊሆኑ የሚችሉትን ነገሮች በትክክል ለመለየት በቀጣይ ጥናት ማድረግ ያስፈልጋል የሚል እምነት አጥኚዋ አላት፡፡ ይሁን እንጂ አጥኚዋ ለልዩነቱ ምክኒያት ይሆናሉ ብላ የምትገምታቸው ነገሮች፦

- የግንዛቤ መለያ ሙከራ ተጠኚ ተማሪው እያነበበ እና የምንባቡን ሀሳብ እየተረዳ የተገደፈውን ቃል ለመሙላት ከፍተኛ የሆነ የማንበብ፣ የመረዳት እናአማራጭ ቃላትን የመጠቀም ችሎታን ስለሚጠይቅ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የቃል ጽህፈት በአብዛኛው በክፍል ውስጥ የተለመደ እና ለአብዛኛው ተማሪ ቅርብ የሆነ ነው ብላ ትገምታለች፡፡
- በሌላ በኩል ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ከለመዱት ምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች በተቃራኒ የግንዛቤ መለያ ሙከራ አማራጭ የሚሰጥባለመሆኑና ለግምት ዕድል የሚሰጥ ባለመሆኑ ሊሆን ይችላል ብላ ትገምታለች፡፡

በዚህ ጥናት በተመዘገበው ውጤት መሰረት በሁለቱም ሙከራዎች ሴት ተጠኚ ተማሪዎች ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት ከወንድ ተጠኚ ተማሪዎች አንጻር በልጦ ተገኝቷል። ሴት ተማሪዎች በግንዛቤ መለያ ሙከራ 54.52 ወንድ ተጠኚ ተማሪዎች ደግሞ 53.26 አማካይ ውጤት አስመዝግበዋል። በቃል ጽህፈት ሙከራ ደግሞ በወንድና ሴት ተጠኚ ተማሪዎች የተመዘገበው አማካይ ውጤት በቅደም ተከተል 64.66 እና 67.82 ነው።

በሁለቱ ምድብ ተጠኚ ተማሪዎች በሁለቱም የተቀናጁ ሙከራዎች ባስመዘገቡት አማካይ ውጤት መካከል የተስተዋለው ልዩነት በትክክል ከግንዛቤ የሚገባና የማይገባ መሆኑን ለማረጋገጥ ውጤቱ በቲ ቴስት (t-test) ቀመር ተሰልቶ ተቀምጧል። በግንዛቤ መለያ ሙከራ ተሰልቶ የተገኘው ዋጋ 0.8509 ሲሆን ይህ ደግሞ ለልዩነት አስተማማኝ መሆን ከሚገባው ልኬት 1.9723 አንጻር አንሶ በመገኘቱ በ9ኛ ክፍል ወንድና ሴት ተጠኚ ተማሪዎች መካከል ከግንዛቤ የሚገባ ልዩነት እንደሌለ ተረጋግጧል።

በሌላ በኩል በቃል ጽህፈት ሙከራ ተሰልቶ የተገኘው የ (t-test) ውጤት ደግሞ 1.8505 ነው። ይህም በሁለቱ ተጠኚ ምድቦች መካከል ያለው ልዩነትአስተማማኝ ነው ብሎ ለመወሰን ከሚያስችለው ዋጋ 1.9723 አንጻር ይህም አንሶ በመገኘቱ እንደ ግንዛቤ መለያ ሙከራ ሁሉ በቃል ጽህፈት ሙከራም ከግምት የሚገባ ልዩነት እንዳልሆነ ማረጋገጥ ተችሏል።

በአጠቃላይ ይህ ጥናት ቀዳሚ ዓላማ አድርጎ የተነሳው የጾታ ልዩነት የአማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድ ያለው ሚና በጮሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የቋንቋ ክሂል ችሎታ ምን እንደሚመስል መመርመር ሲሆን ጥናቱ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ካገኘው መረጃ መረዳት እንደተቻለው በአማርኛ ቋንቋ አጠቃላይ ብቃት አንጻር የጾታ ልዩነት ከቁጥር የሚገባ ሚና የለውም። ይህም ከዓመታት በፊት በፋንቱ ደምሴ በ 1989 ዓ.ም. በ11ኛ ክፍል ወንድና ሴት ተማሪዎች ላይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ስነ ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ካቀረበችው ጥናት ውጤት ጋር የዚህ ጥናት ግኝት ተመሳስሎ አለው።

## 5.2. አስተያየት

ይህ ጥናት ያነሳቸውን ጥያቄዎች ለመመለስ ካለፈባቸው ሂደቶችና በመጨረሻም በጥናቱ ከተገኘው ውጤት ማጠቃለያ በመነሳት አጥኚዋ የሚከተሉትን አስተያየቶች አስቀምጣለች።

- በዚህ ጥናት ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋሉት የመመዘኛ ስልቶችና ውጤቶቹ የተሰሉበት ቀመሮች ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተብለው የተዘጋጁ በመሆናቸው በዚህ ጥናት ውስጥ በቀጥታ ለመጠቀም አስገዳጅ ሆኗል። ይህም የሆነበት ምክኒያት በአማርኛ ቋንቋ የተቀናጁ

ሙከራዎች የሚሰሉበት እራሱን የቻለ ቀመር ባለመኖሩ ነው። በዚህም የተነሳ የአንዱን መስፈርት ለሌላ ቋንቋ በቀጥታ መጠቀሙ በተወሰነ ደረጃ በጥናቱ ሂደትና ውጤት ላይ የራሱ የሆነ ክፍተት ሊያመጣ ይችላል።

- የተቀናጁ ሙከራዎች የተማሪዎችን አጠቃላይ የቋንቋ ብቃትን በመመዘን ደረጃ ሁነኛ መሳሪያዎች እንደሆኑ የተለያዩ ጥናቶች ይጠቁማሉ። በዚህ ረገድ ለመማር ማስተማር ተብለው የሚዘጋጁ የመማሪያ መጻህፍት የተማሪዎችን አጠቃላይ የቋንቋ ብቃትን ለማሻሻል የሚረዱ የየክፍል ደረጃውን የሚመጥኑ መልመጃዎችን በበቂ ሁኔታ ቢያካትቱ መልካም ነው።

- በቃል ጽህፈት በሁለቱም ጾታዎች የተገኘው ውጤት ከግንዛቤ መለያ ሙከራ ከተገኘው ውጤት የላቀ ነው። ለዚህም ምክኒያት ሊሆን ስለሚችለው መንስዔ መላምት ከመሰንዘር ውጪ የተረጋገጠ ምክኒያት ማቅረብ በዚህ ጥናት አልተቻለም። ምክኒያቱም ይህ የጥናቱ ዓላማ ባለመሆኑ። ስለዚህ በዚህ ደረጃ ያለውን ክፍተት ለመሙላትና ምክኒያቱን በትክክል ለማረጋገጥ በቀጣይ ራሱን የቻለ ጥናት ቢደረግበት መልካም ነው።

# ዋቢ ጽሁፎች (Bibliography)


አራጋው ሽባባው::(2003):: *በአማርኛ ቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደትበራስመተማመን(Self Esteem) ያታና የትምህርት ውጤት ተዛምዶ::* ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ:: ያልታተመ::

እንድሪስ አባይ::(2000):: *የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን መማር ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ::* ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ::ያልታተመ::

ግዛቸው በላይ::( 2007):: የጾታ ልዩነት የአማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድ ያለው ሚና በአባይ ምንጭ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ ቤት በ 10ኛ ክፍል ተማሪዎች የቋንቋ ክሂል ችሎታ ላይ ያተኮረ ጥናት:: ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ:: ለማስተርስ ዲግሪ ሟሟያ የቀረበ ጥናት:: ያልታተመ

ፋንቱ ደምሴ:: (1989)::*የጾታ ልዩነት አማርኛ ቋንቋን በመማር ረገድ ያለው ሚና በእንጦጦ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች አጠቃላይ የቋንቋ ብቃት ላይ የተካሄደ ጥናት::አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ::* ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት:: ያልታተመ::

Adem. M. and Gebre. B. (1990). *The Impact of Objective Type Tests on the Learning Process of High School Mathematics*. The Ethiopian Journal of Education, 11 : 28-49.

Anderson, M.L. (1988). *Thinkign about Women; Socialogical Perspective on sex and Gender,* Second Educaiton. London: Macmillan Publishing Company.

Anderwood. (1989). *A Technique for Measuring Reading Comprehension and Readability.*English Language Journal. 178-181.

Anker, R. (1998)*. Difference between Sex and Gender.In Gender and Jobs*. Oxford Internatioanl labour orgnaizaiton.

Balair, H. and Sanford, K. (1999).*Boys will be boys expanding letracy horizinse for boys. National council of teachers of English*.

Benbow, C. and J.C. Stanely, (1983). *Sex Differences in Mathematical Resoning Ability: More Facts".* In Psychology of women: Selected Reading S. Williams, H. Juanita. (ed).

Betz, Nancy and Louise. F. Fitzegerald. (1987). *The Career Psychology of Women*. Academic Press, Inc.

Blumberg, B., Cooper, D. R., & Schindler, P.S. (2005). *Business Research Methods*. Berkshire: McGrawHill Education.

Cameron, Deborah. (1985). *Feminism and Linguistic Theory*. The Macmillan Press, Ltd.

Carroll, John B. (1961).*The psychology of language testing*. In Alan Davies (Ed.), Language testing symposium: A psycholinguistic approach. London: Oxford University Press. Chapter 4, pp. 46-69.

Carroll, J. B. (1961/1972). *Fundamental considerations in testing for English language proficiency of foreign students.* In H. B. Allen & R. K. Campbell (Eds.), Teaching English as a second language, New York: McGraw-Hill. (Reprinted from Testing the English proficiency of foreign students [1961]. Washington, DC: Center for Applied Linguistics.)

Clark, Ann and Trafford. *Boys into Modem Languages: an investigation of theDiscrepancy in Attitudes and Perfonnance between boys and girls in ModemLanguages*. *Gender and Education.* 7/3: 315-325.

Cronbach, L. J. (1951). *Coefficient alpha and the internal structure of tests. Psychometrika*, 16(3), 297-334

Datnow, A. and Hubbard, L (2002). *Gender in Policy and practice: Perspectives on single-sex and Co-educational schooling*. New York; Routledge Flarmer.

Davies, Alan. (1988). *Communicative Language Testing*. In Testing Engish forUniversity Study*.* Arthur Hughes. (ed.), Longman.

Ebel, R. (1999). *Encyclopaedia of Educational Research*. Toronto: Engros.

Evans, J. D. (1996).*Straightforward statistics for the behavioral sciences*. Pacific Grove, CA: Brooks/Cole Publishing.

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Education (2019). *Education Statistics* Annual Abstract 2011 E.C.

Fouley, K. and Garry. A. Ziko. (1985). *Detennining the Reliability, Validity and Scalability of the Graduate Dictation Test*. *Language Learning.* 35/4:555-565.

Genet Zewdie, (1991) "*Women in Primary and Secandary Educaiton.*"In Gender Issues in Ethiopia.

Gentry, J.L.(2006) . *Comparision of the effects training expositer text*.

Gililand, John.(1975). Readability. Londen: Hadder and stoutgton.

Global Partnership for Education. (2021). *Gender Equality.* Global Partnership for Education. Retrieved from: https://www.globalpartnership.org/what-we-do/gender-qualitity?fbclid=IwAR0PfioFLdrBkLVnMIC6YVwzEc6XqDxTrJf7VnVdjO0XEQ16Jj2s0en7Fs

Gunning,R.(1969). The Fog Index after twenty years journal of business communication,6(2),3-13.http:doi.org/10.1177/002194366900600202.

Haregewoin Cherinet and Yusuf Orner Abdi. (1994). *Facilitating Assertiveness Among College Students*: Students' Manual. Addis Ababa.

Heton, J. (1975) *Writing English Lanauge Test*. London: Longman.

Heton,J.(1990) Classroom Testing.longman Group. Ltd.

Hilton, Thomas. and G. Berglund. (1974). *Sex Differences in Mathematics Achievment*. A longitudinal study. *Journal of Educaitonal Research*.67/5: 231-237.

Hirut Tafere. 2002. *"Violence against Women from Gender and Cultural perspectives."* Refleciton: Noy Doccumentaiton of Panos Ethiopia: Master Printing press.

Hughes, A. (1989). *Testing for Language Teachers*. Cambridge and New York: Cambridge University Press ix + 172 pp. ISBN 0-521-27260-2.

Imani, Swilla. (1993). *Gender in equalities in the teaching Staff of boys and girls Secondary Schools in Tanzania*. Research report.

Johnes, L. and T. smart. (1995). *Confidence and Mathematics: A Gender Issue?* Gender and Education. 7/ 2 : 157-166 .

Kuder, G. F. & Richardson, M. W. (1937). *The Theory of the Estimation of Test Realiability*. Psychometrika, 2(3), 239-270.

Lindsey, L.L. (2005).*Gender Roles: A sociological perspecitive*. New Jersey: Prentice Hall.

Lott, Bernice. (1987). *Women's Lives Themes and Variations in Gender Learning*. Monterey. California: Brooks and Cole.

Mackey, Wiliams Francis. (1965). *Language Teaching Analysis*. London: Longman.

Macoby.E.E. and Jackline C.N. (1974).*The Psychology of sex Differences*. Stanford. CA: Stanford Unviersity.

Marsh, Herbert. (1989). *Effects of Attending Single Sex and Co-educaitonal High Schools on Achievement, Attitudes, Behaviours, and sex differences.* Journal of *Educaitonal Psycholog*y.81/1: 70-85.

Morris, S. (1983).*Dictation a Technique in Need of Reappraisal*. *ELT* journal .37:2.

Nation, P. (1991).*Dictation, Dicto — Compand related techniques*.English teaching forumjournanal .19:4

Nwana, O.C. (2007). *Textbook on Educational Measurement and Evaluation*. Owerri: Bomaway publishers.

Oller, J. Jr. (1971). *Dictation as A Device for Testing Foreign Language Proficiency*.English Language Teaching Journal. 25/3:254-259.

Oller,J.,Jr. (1972) “Scoring Methods and Difficulty Levels For Cloze test of English LanguageProficiency”. Modern Language Journal. 50 : 151-158.

Oller, J., Jr. and V. Streiff. (1975). *Dictation A Test based Expectancies*. EnglishLanguage Teaching. 30: 25-36.

Oller, J., Jr (1979). Language Test at School. Longman Group Ltd.

Olson, C. Millard. (1979). *Individual Difference*: A Precious Asse. Educational Leadership.xxIII/17: 140-147.

Olson, D.H. (2000). *Gender Roles.Imarriage and the Family Diversity and Strengths*.Third Edition.Torto: May field publishing Company.

Oxford, R. (1990). *Language learning strategies: what every teacher should know*. Heinle & Heinle Publishers.

Papalia, D.E. and et al. (1999). *A child's World*. Toronto: McGraw.Hill.

Patric, G.T.W. (1985). *The Psychology ofWomen*. In Psychology of Women Selecitng Readings. Williams E. Juanita. ed.

Patricia, I. & et al. (1974). *Cloze, Dictation and the Test of English as a Foreign Language*.

Piyanu kool, S. (2001).*Effectsof Teaching Reading through Discussion of Text Stracture.*

Roson, C. Bernard. (1989). *Women Work and Achievement. Hongkong*: The Macmillan Press. Ltd.

Santrock, J.W. (2001)*. Educaitoanl Psychology*. California: McGraw Hill Companies.

Seyoum Tefera. (1991). *The Participation of Women in Higher Education In Ethiopia*. In Gender Issues in Ethiopia. Tsehay Berhane Selassie (ed).

Stansfield, CW.(1995). *A History of Dictation in Foreign Language Teaching and Testing*.The modern languge Journal 69:2

Subbo, W. (2002). T*he Conceptualizaiton of Gender. Perspectives on Gender Discourse*: Gender and Constituions Marking in Kenya. Nirboi: Heinirch Hall Foudaiton.

Suzanne, W. 2002.*The Oxfam Gender TrainingManual*.TOKYO Oxfam Pirnt Unit.

Tannen, D. (1992). *You just do not understand*. New York: William Morrow.

Taylor, D. (1993). *From the child's point of view*. Portsmouth, NH: Heinemann

Tebebe Alemayehu.(1987). *An Exploration of the English Language ProficiencyLevel of Government and Mission Secondary School Levels*. M.A. Thesis.Addis Abeba University.

Tsegie Haile. (1991). *An Assessment of the Academic Performance of Female Students in Higher Educational Institutions in Ethiopia*. The Case of AAU. OSSREA, Addis Ababa.

Warrick, D. Pamela and Jack. A. Naglieri. (1993). Gender Difference in Planning, Attention, Simultaneous and Successive (PASS) Cognitive Processes.*Journal of Educaitonal Pscyhology* 85/4: 693-701.

Weir, Cyril. (1990). *Communicative Language Testing.* Prentice Hall International.

Williams, H. Juanita, (ed.). (1985)*. Psychology of Women* 3rd (ed.). New York: W. W.Norton

Xiufang Xia (2013). *Gender Differences in Using Language.* Theory and Practice in Language Studies, Vol. 3, No. 8, pp. 1485-1489. Finland.

## አባሪ ሀ-1

### አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

### የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

**የግንዛቤ መለያ ሙከራ መመሪያ**

የዚህ የግንዛቤ መለያ ሙከራ ተቀዳሚ ዓላማ በ2015 ዓ.ም. በጮሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክሂል ችሎታ አንጻር በወንድና ሴት ተማሪዎች መካከል ልዩነት መኖር አለመኖሩን የሚያረጋግጥ መረጃ መሰብሰብነው፡፡

ውድ ተማሪዎች፦ ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ ውስጥ የተገደፉ ቃላት አሉ፡፡ የተገደፉት እያንዳንዱ ቃላት ቁጥር ተሰጥቷቸዋል፡፡ ማለትም በምንባቡ ውስጥ ቁጥር ተሰጥቷቸው የሚገኙት ክፍት ቦታዎች በዚህ ቃል ምትክ የገቡ ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ክፍት ቦታ ለአንድ ቃል ብቻ የቆመ ነው፡፡በመሆኑም ለምንባቡ በይበልጥ ተስማሚ የሆነና በዚህ ቦታ ሊገባ የሚችል ቃል መምረጥና በተሰጠው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ማስፈር ያስፈልጋል፡፡ከሁሉ ቅድሚያ ግን የምንባቡን ሃሳብ ለመረዳት ይቻል ዘንድ ፅሑፉን በጠቅላላ አንድ ጊዜ ማንበብ ተገቢ ይሆናል፡፡

ስለሙከራው አሰራር በይበልጥ ለመረዳት ከታች የቀረበውን ምሳሌ መመልከት ይጠቅማል፡፡ውድ ተማሪዎች ተነጋግሮ መስራት አይቻልም በተመሳሳይ ፣ስም መፃፍም አይቻልም፡፡ውድ ተማሪዎች፦ ጊዜያችሁን ሰውታችሁ ሙከራውን ለመሥራት ፈቃደኞች በመሆናችሁ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

**<u>አስረጅ</u>**

ሰዎች በተፈጥሯቸው በማህበራዊ ህይወታቸው ንቁ ተሳታፊዎች ናቸው፡፡ በዚህም 1_____________ ለማህበራዊ ግንኙነት ማሳለጫ ይረዳቸው ዘንድ የተለያዩ 2____________ ይፈልጋሉ፡፡ ለዚህም የተለያዩ ዘመናዊ የመገናኛ አውታሮችን 3______________፡፡ ከተፈጠሩትም መካከል በተሻለ 4_____________ የሆነ አሰራር ጠቃሚ መሆኑን ተገንዝበው ትኩረታቸውን ወደዚያ 5___________ ይገኛሉ፡፡

መልስ

1. ምክንያት  2. መንገዶች3. ፈጥረዋል 4. ዲጂታላይዝ 5. እያደረጉ

# አባሪ ሀ- 2

## የግንዛቤ ሙከራ 1

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅየአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

በተቀመጥኩበት ኣሻግሬ አካባቢው ላይ የሚገኙትን ሱቆችና ቡና ቤቶች ማስተዋል ቀጠልኩ፡፡ አንዳንዶቹ ሱቆች የምሽቱን መምጣት ምክንያት በማድረግ 1 _____ ነው፡፡ በሁለት ቡና ቤቶች የበር መስታወት ብልጭ 2_______የሚል ህብረ ቀለማት ብርሃን እስክስታ 3 _____ ይታያል፡፡ ለእነዚያ ቡና ቤቶች ቀኑ ገና 4------ነው፡፡ ለእኔ ግን መሽቷል፡፡ እንቅልፌም ከመጣ እዚሁ ጋር ጥቅልል ብዬ 5________፡፡ እስካመንኩበት ድረስ የትም ልሁን የት መጪው 6_______ እኩል ያልፋል፡፡ መጪውንም ንጋት እኩል እቀበለዋለሁ፡፡ ታዲያ ከባዱ ነገር የቱጋር ነው? 7_______ ነበር፡፡ እውነትም ይኸው ሌሊቱ ለሁላችንም እኩል 8----------- ያንን የምሽት ግርግር በማለዳ ብርሃንም ለማየት 9-----------፡፡

‘ይሄንን የህዝብና የክንውን እንቅስቃሴ ቁጭ ብዬ 10_____ ሳይሆን፣ የዚህ እንቅስቃሴ አንድ አካል ለመሆን ነው 11________ የደረስኩት፡፡ እናም ተነስቼ ከዚህ የክንውን ጅረት ጋር በአንድ 12________አለብኝ፡፡’ ብዬ አሰብኩና ከተቀመጥኩበት ተነስቼ 13________ እምብርት ነው ብዬ ወዳሰብኩት አቅጣጫ መንገድ 14_________፡፡

የተንዝኩት የንግድ ቤቶች ይበልጥ ወደሚበዙበት 15______ነበር፡፡ ሆዱ የተርቤአለሁ መልእክቱን ትናንት ማምሻዉን ካቆመበት 16______፡፡ እንግዲህ የሆድን ረሃብ ለማስታገስ ያለው አማራጭ 17______ ነው፡፡ ቢቻል ማንኛውንም ፈጣን ስራ ሰርቶ ለጥሪው 18______ መድረስ፤ ይሄ ካልሆነም እርቦኛል ብሎ ከአንዱ ምግብ ቤት 19 __________ መለመን ነው መፍትሄው፡፡ በተረፈ መጨነቅና ተስፋ መቁረጥ እርባና 20_________፡፡

ድንገት አይኖቼ አንድ አጭር ራሰ በረሃ 21________ ላይ አረፉ ፡፡ከአንድ ሱቅ በር ላይ ቆሟል ፡፡ እግሩ ስር በማዳበሪያ ከረጢት የተቋጠረ ሸክም 22________፡፡ በአይኖቼ ግራና ቀኙን ሲቃኝ 23_______ ሰው ፈልጎ እንደሆነ እሰብኩና 24 _________፡፡

“ጋሽዬ፣ የሚሸከም ፈልገው ነው?” 25______ በትህትና፡፡ ከአነጋገሬ ነው መሰል ሽቅብ 26______፣“አዎ፣ ትሸከማለህ?” ብሎ ጠየቀኝ፡፡ ከዚህ በፊት ክብደት ያለው ነገር ተሸክሜ 27______፣ ሸክሙ እንደማይከብደኝ ራሴን 28_________፤ “አዎ፡፡” አልኩት፡፡

“በል፣ እዚያ መኪና ላይ 29_____ጫንልኝ፡፡” ብሎ ጎዳናዉን ተሻግሮ የቆመ 30______ አሳየኝ፡፡ ሸክሙን ብቻዬን ለማንሳት ስንደፋደፍ በትኩረት አየኝና 31_________ በኩል አግዞ አሸከመኝ፡፡ “የአምላክ ያለህ ፡፡ አልኩኝ ለራሴ ብቻ በሚሰማ 32_____፡፡ ‘ ይሄማ ዝሆን ነው፤ ግን ደግሞ መድረሻው 33_______ ነው፡፡’ ብዬ ተፅናናሁ ፡፡

ሸክሙ እያንደረደረ ጎዳናዉን አሻገረኝና 34_______ጋር ደረስኩ፡፡ የሚከብደዉን ሸክም የእቃ መጫኛው ላይ ለማስቀመጥ 35________ ትከሻዬን ሳዘነብል ‘ዝሆኑ’ ከላዬ ላይ 36________ መኪናው ላይ ክፉኛ ዘጭ አለ፡፡ “አንተ!... ምናባቱ ይሄ!... ያባትህ ንብረት መሰለህ 37________?” አለኝና ተንጠራርቶ በጥፊ አጮለኝ፡፡ የወገቤ ህመም ላይ የጥፊው 38_______ሲጨመርበት ባለማመንና በድንጋጤ አይኖቼ 39_________፡፡ የሰውየው አይኖች ግን በንዴት40_______ ፈጠዋል፡፡

ምንጭ(ዓለማየሁ ደመቀ) ፡፡ 2013 ፡፡ዮቶር(ኮብላይ ካህን) ገፅ 85- 87)

## አባሪ ሀ- 3

### የግንዛቤ ሙከራ 2

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍል ትምህርት**

የሃምሌ ክረምት ምድሪቱን አለምልሟታል። ጨሌ እየጋጡ የሚቦርቁ እንቦሳ 1_______በብዛት ይታያሉ። እርሻው ተንጣሎ ሲታይ አረንጓዴ የፋርስ ምንጣፍ 2_____ ይምስላል። አበቦች ፈክተዋል። በአጠቃላይ በሬሳ ውበትን እንደ 3_____ ተከናንባ እንደ ካባ ደርባ አምራ ትታያለች። የበጋው ፀሃይ ንዳድ ያሳረረው ደን የጠወለጉ 4_______ እያራገፈ በምትኩ አዳዲስ ቀንበጦችን እያለመለመ ክረምትን 5_____ደህና ወጣሽ ለማለት በደስታ 6_____ ይመስላል። አእዋፍ በአይነትና በብዛት በየህብረ ቀለማቸው አሸብርቀው7_____ላይ ሲያንዣብቡ፣ በጣፋጭ ዝማሬያቸው አየሩን እየሰነጠቁ8_____ ልብን ይማርካሉ፣ የፈጣሪን ድንቅና ረቂቅ ጥበብ 9_____። አምላክ እንኩዋንስ ጣፋጭ ዝማሬን በሚያሰሙ አእዋፍ ላይ 10_____ ድምፅ የሌላቸውን አበቦች እንኩዋን በብዛታቸው መጠን 11____ ድንቅ ውበት አላብሷቸው ሲታዩ ይህቺን ምድር ምን ያክል አሳምሮ እንደሰራት በቂ ማረጋገጫ ነው። የሰው ልጅ ተንከባክቦ ቢያቆያት ገነት የሆነች 12______... የጌትነት መኩሪያ መንደር ይህ የአምላክ ገፀ በረከት 13______የጎበኛት ትመስላለች። ተፈጥሮን እያደነቀች ፍልቅልቅ እያለች 14_______ ላይ ትገኛለች። ለዚህ ደግሞ የረሰረሰው ዉበቷ ዐቢይ ምስክርነቱን 15_____ ነው። የክረምቱ ወዝ እንደ ቅቤ አርሷታል የደስደስ 16_______።

እንደ መንደሪቱ ውበትን ያልተላበሰችው ከአበቦቹ ጋር 17______ ያልፈካችው የጌትነት እናት ብቻ ነች። ለደቂቃ ከዐይኗ እንዲርቅ የማትፈልገው ልጇ ሳትወድ 18______ ተለይቷት ወደማያውቀው አገር ከሄደ ሶስተኛ ወሩን 19_____ነው። ከዛሬ ነገ ምን እሰማ ይሆን? እያለች 20_____ በሰቀቀን ገላዋ አልቋል። ትንሿ ልጇ ዘይኑ አጠገቡዋ ባትኖር ኖሮ 21_______ ይቋረጥ ነበር። ነጋ ጠባ በዐይኗ ላይ 22______ የልጇ ነገር ብቻ ነው። አቶ አለሙ እንደነገሩዋት ከሆነ አዲስ አበባ ቀማኛና 23_______የበዛበት፣ የህዝብና የመኪናው ቁጥር እኩል የሆነበት፣ 24______፣ ምስቅልቅል ያለ ከተማ ነው። ይህንን ስለሰማች ልጇ ስራ ፍለጋ ሲንከራተት፣ 25______፣ ከአንዱ ወደ አንዱ ሲሮጥ... መንገድ ሊያቋርጥ 26_____መኪና ሲገጨው...

በግንባሩ ሲወድቅ… ከዚያም አንድ 27______የሚያውቀው ዘመድ ጠፍቶ ደሙ ያለማቋረጥ 28_______ እንደጎርፍ ሲወርድ… "እማዬ!! እማይዬ… ድረሺልኝ!!" እያለ 29________፣ በየመንገዱ ላይ የሚተራመሰው ህዝብ ግራና ቀኙን 30_______ አፉን እየያዘ "አይ ሚስኪን ከየት የመጣ ይሆን" እያለ ከንፈሩን 31_________ የሚያድርበት ቦት አጥቶ በየበረንዳው ሲንከራተት፣ የለበሰው 32_______ በላዩ ላይ አልቆና ቆሽሾ ሲቀምል፣ የሚበላው 33_______ በረሃብ ሲሰቃይ…ይሄ ብቻ ነው የሚታየው፡፡ "እንደ እናቴ ሳይሆን እንደሚስቴ አዉለኝ" የሚባለው ለዚህ አይደል? ሚስት ባሏ ከፊቷ ዞር ካለ ከሌላ 34_______ ጋር አለሙን ሲቀጭ… ሲቀብጥ… 35________ ሲቆርጥ፣ ጨርቅ ሲጋፈፍ… ሲፈነጥዝ… ሲዳራ ነው የሚታየው፡፡ የእናት ግን ከዚህ ለየት ያለ በመሆኑ 36_________ ማረፊያ፣ የባሏ ትካዜ ማስረሻ፣ የልቧ ኩራት 37_______ መመኪያ ተስፋዋ የሆነው ልጇ እሷን ለመርዳት 38________ አገር እንደወፍ ብርር ብሎ በሄደበት ምን 39_________ ማወቅ ባለመቻሏ ክፉ ክፉውን ብቻ እያሰበች40________ መነመነች፡፡

ምንጭ (ትክክል ገና፡፡ 2012 ፡፡ የተወጋ ልብ ገፅ 91- 92)

# አባሪ ሀ-4

## የግንዛቤ ሙከራ 1- መልስ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

### የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና የኮሚዩኒኬሽን

### ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

<u>የግንዛቤ ሙከራ 1-መልስ</u>

1. እየዘገ
2. ድርግም
3. ሲወርድ
4. መወለዱ
5. እተኛለሁ
6. ሌሊት
7. ብዬም
8. ነጋና
9. በቃሁኝ
10. ለመታዘብ
11. እዚህ
12. መፍሰስ
13. የከተማዋ
14. ቀጠልኩኝ
15. መንገድ
16. ቀጠለ
17. ሁለት
18. በፍጥነት
19. ትርፍራፊ
20. የለውም
21. ሰው
22. ተጋድሚል
23. የሚሸከምለት
24. ተጠጋሁት
25. አልኩት
26. ተመለከተኝ
27. ባላውቅም
28. አሳመንኩትና
29. ወስደህ
30. መኪና
31. ከአንድ
32. ድምጽ
33. ቅርብ
34. መኪናው
35. ግራ
36. ተወርውሮ
37. የምታሽቀነጥረው
38. ህመም
39. ፈጠጠ
40. ይበል

# አባሪ ሀ-5

## የግንዛቤ ሙከራ 2- መልስ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና

## የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

<u>የግንዛቤ ሙከራ 2-መልስ</u>

1. ጥጃዎች
2. የለበሰ
3. ሽማ
4. ቅጠሎቹን
5. እንኳን
6. የሳቀ
7. በሰማዩ
8. ሲያደምቁት
9. የመሰክራሉ
10. ይቅርና
11. የየራሳቸውን
12. ምድር
13. በሰፊው
14. በመሳቅ
15. እየሰጠ
16. አላብሷታል
17. አብራ
18. በግድ
19. እያስቆጠረ
20. በትካዜና
21. እስትንፋሷን
22. የሚንቀዋለለው
23. ሌባ
24. ትርምስምስ
25. ሲባዝን
26. ሲል
27. እንኳ
28. ሲፈስ
29. ሲጮህ
30. ከቦት
31. ሲመጥለት
32. ልብስ
33. አጥቶ
34. ሴት
35. ጮማ
36. የአይኖቿ
37. ምንጭ
38. ወደማያውቁት
39. እንዳጋጠመው
40. በሃሳብ

# አባሪ ለ-1

## የቃል ዕህፈት ሙከራ 1

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጋዜጠኝነት እና

## የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

<u>የቃል ጽህፈት ሙከራ 1</u>

አንድ አራት ወር እየተመላለስኩ እዛው ዩኒቨርስቲው አካባቢ ቤት ተከራይቼ ለመማር ወሰንኩ። ምንም አስቤ ሳይሆን የአዲስ አበባ ታክሲ ጊዜዬን እየበላብኝ ስለተቸገርኩ ነበር። ማንም አልተከራከረኝም፣ ዩኒቨርስቲው ከሚወረዉሩልኝ ሳንቲም ላይ ቤተሰብ በየወሩ ድጎማ እየመረቀበትድክም ያለች ቤት አንድ ሰፈር ዉስጥተከራየሁ። እንግዲህ የእኔ ቤትና ከጎኔ ያሉት ጭርንቁስ ቤቶች በመደዳ የተሰለፉ ነበሩ። ፊት ለፊት ደግሞ ፊታቸውን ወደ እኔ ቤት ያዞሩ በስሪቱም፣ በመጠንም ከእኔ ቤት ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ሌላ መደዳ ቤቶች አሉ። መስኮቴን ስከፍት ፊት ለፊት ያለው ቤት ጋር እፋጠጣለሁ። በሬን ስከፍት ፊት ለፊት ካለ በር ጋር!! በሁለት መደዳ ቤቶች መካከል ቀጭን የእግር መንገድ አለች። የእኔ ቤትና ፊትለፊቴ ያለው ቤት ጣራቸው ሊገጣጠም ምንም ያህል ስለማይቀረው በመካከላችን በቀጭኗ የእግር መንገድ የሚያልፍ ሰው ረዥም ኮሪደር ውስጥ የሚያልፍ ሊመስለው ይችላል። ከበሬ ላይ አንድ ጠቀም ያለ ርምጃ ወደፊት ብራመድ ፊት ለፊት ያለው ቤት በር ላይ አርፋለሁ፤ ይሄ ነው የተከራየሁት ቤት።

ምንጭ [አሌክስ አብረሃም። 2012. ዶክተር አሸብርና ሌሎችም ገፅ 103]

## አባሪ ለ-2

### የቃል ዕህፈት ሙከራ 2

### አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

### የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና

### የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

እማማ በለጡ የሽሮ ክክ ጸሀይ ላይ ካሰጡ እሳቸው ሳያዩ እኛ ዘግነን እንደምንቅም ያውቃሉ፡፡ ስለዚህ ክካቸውን ሲያሰጡ የምንጫወተውንም ልጆች ሆነ በየቤታችን የለነውንም በሙሉ ጠርተው ይሰበስቡናል፡፡ ሳቂታ ናቸው ሲቆጡም እየሳቁ ነው፡፡ በገጣጣነታቸው ትልልቅ ሰዎች በለጡ ገጦ ይሏቸዋል፡፡ ልጆች ግን እማማ ብልጦ ነው የምንላቸው፡፡ወደ ክካቸው እያሳዩን ተመልከቱ ይህ ክክ የእጣኑ ቂርቆስ ጠበል ጠዲቅ የማደርግበት የስለት ክክ ነው፡፡ አሁን እኔ አስጥቼ ሳላየው ዘግኖ የበላ ልጅ ወዮለት፡፡ እኔ ባላየው እጣኑ ቂርቆስ ስለሚያየው ተቆጥቶ ሆዱን አሳብጦ ፈስ በፈስ አድርጎ ነው የሚገለው፡፡ ስለዚህ እንዳትቀሰፉና እኛንም ከፍተኛ ሀዘን ላይ እንዳትጥሉን አደራ እንዳትዘግኑ፡፡ ላልሰሙት የሰፈር ልጆች ሁሉ ንገሯቸው ይሉና ትንሽ ትንሽ ክኩን ቆንጥረው ይሰጡናል፡፡ መኩዬ ቀጫጫው ፈርቶ ሲያፈገፍግ አይዞህ አሁን ብላ እኔ ስለሆንኩ ቆንጥሬ የሰጠኋችሁ እጣኑ ቂርቆስ ምንም አይልም ይሉን ነበር፡፡ ልጆች ሳለን ትልልቅ ሰዎች የመከሩንን እንሰማለን የሚነግሩንን ሁሉ እንደ ህግ እናከብረዋለን፡፡

ምንጭ፤- ልጅነት፡፡ ደራሲ፦ ዘነበ ወላ፡፡ 2000 ዓ.ም፡፡ገጽ 31

# አባሪ ሐ-1

## የግንዛቤ ሙከራ መልስ መስጫ ወረቀት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂውማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት የጋዜጠኝነት እና

## የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

ጾታ________________

በምንባቡ ውስጥ ላሉት ክፍት ቦታዎች በይበልጥ ተስማሚ ይሆናል ያላችሁትን ቃል በምንባቡ ውስጥ ባለው ተራቁጥር መሰረት ከታች ከተሰጠው ቦታ ላይ አስፍር/አስፍሪ።

1. ______________________
2. ______________________
3. ______________________
4. ______________________
5. ______________________
6. ______________________
7. ______________________
8. ______________________
9. ______________________
10. ______________________
11. ______________________
12. ______________________
13. ______________________
14. ______________________
15. ______________________
16. ______________________
17. ______________________
18. ______________________
19. ______________________
20. ______________________
21. ______________________
22. ______________________
23. ______________________
24. ______________________
25. ______________________
26. ______________________
27. ______________________
28. ______________________
29. ______________________
30. ______________________
31. ______________________
32. ______________________
33. ______________________
34. ______________________
35. ______________________
36. ______________________
37. ______________________
38. ______________________
39. ______________________
40. ______________________

ጠቅላላ ውጤት ________________

# አባሪ ሐ-2

## የቃል ጽህፈት መልስ መስጫ ወረቀት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና

## የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅየአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

ጾታ ____________

ውድ ተማሪዎች በዚህ የቃል ፅህፈት ሙከራ ለመሳተፍ ውድ ጊዜያችሁን ሰውታችሁ መልካም ትብብራችሁን ስላደረጋችሁልኝ ምስጋናዬ የላቀ ነው።

መመሪያ፡ ውድ ተማሪዎች፤ ከዚህ ቀጥሎ በትክክል አዳምጣችሁ የምትጽፉት የቃል ጽህፈት ሶስት ጊዜ ይነበብላችኋል። በመጀመሪያው ንባብ ምንም ሳትጽፉ በሚገባ በጥሞና አዳምጣችሁ የምንባቡን ሀሳብ ለመረዳት ትሞክራላችሁ።ምንባቡ ዘለግ ባለ ፍጥነት ሁለተኛ ጊዜ ሲነበብ ያዳመጣችሁትን በሙሉ ቃል በቃል መጻፍ ይጠበቅባችኋል። ምንባቡ ለሶስተኛ ጊዜ በተለመደው የንባብ ፍጥነት ሲነበብ በቃል የጻፋችሁት ጽሁፍ ውስጥ ያልተሟላ ካለ የማሟላትና የተሳሳተ ካለ የማስተካከል ጊዜ ይኖራችኋል።

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------

ድምር ____________________

# አባሪ መ-1

## የወንድ ተማሪዎች የግንዛቤ መለያ ሙከራ ውጤት

| ተ.ቁ | የተገኘው ውጤት ከ10%ና የሙከራው አይነት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የግንዛቤ መለያ ሙከራ | | | | | | |
| | ከ100% | ተ.ቁ | ከ100% | ተ.ቁ | ከ100% | ተ.ቁ | ከ100% |
| 1 | 66 | 26 | 40 | 51 | 47 | 76 | 65 |
| 2 | 48 | 27 | 39 | 52 | 65 | 77 | 52 |
| 3 | 45 | 28 | 42 | 53 | 55 | 78 | 53 |
| 4 | 61 | 29 | 50 | 54 | 45 | 79 | 51 |
| 5 | 34 | 30 | 52 | 55 | 71 | 80 | 75 |
| 6 | 52 | 31 | 47 | 56 | 56 | 81 | 61 |
| 7 | 54 | 32 | 49 | 57 | 68 | 82 | 64 |
| 8 | 39 | 33 | 61 | 58 | 74 | 83 | 71 |
| 9 | 49 | 34 | 51 | 59 | 53 | 84 | 49 |
| 10 | 49 | 35 | 36 | 60 | 40 | 85 | 69 |
| 11 | 53 | 36 | 50 | 61 | 57 | 86 | 46 |
| 12 | 57 | 37 | 54 | 62 | 72 | 87 | 63 |
| 13 | 44 | 38 | 52 | 63 | 45 | 88 | 44 |
| 14 | 65 | 39 | 42 | 64 | 55 | 89 | 65 |
| 15 | 59 | 40 | 51 | 65 | 51 | 90 | 55 |
| 16 | 41 | 41 | 44 | 66 | 70 | 91 | 49 |
| 17 | 42 | 42 | 45 | 67 | 62 | | |
| 18 | 53 | 43 | 41 | 68 | 51 | | |
| 19 | 62 | 44 | 49 | 69 | 57 | | |
| 20 | 51 | 45 | 52 | 70 | 87 | | |
| 21 | 39 | 46 | 65 | 71 | 41 | | |
| 22 | 50 | 47 | 49 | 72 | 43 | | |
| 23 | 57 | 48 | 60 | 73 | 49 | | |
| 24 | 55 | 49 | 51 | 74 | 37 | | |
| 25 | 64 | 50 | 59 | 75 | 41 | | |

## አባሪ መ-2

### የወንድ ተማሪዎች የቃል ጽህፈት ሙከራ ውጤት

| ተ.<br>ቁ | የተገኘው ውጤት ከ100%ና የሙከራው አይነት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የቃል ጽህፈት ሙከራ | | | | | | |
| | ከ100% | ተ.ቁ | ከ100% | ተ.ቁ | ከ100% | ተ.ቁ | ከ100% |
| 1 | 60 | 31 | 72.5 | 61 | 70.5 | 91 | 62.5 |
| 2 | 45 | 32 | 69.5 | 62 | 60.5 | | |
| 3 | 68 | 33 | 76.5 | 63 | 65.5 | | |
| 4 | 50 | 34 | 56 | 64 | 77 | | |
| 5 | 60 | 35 | 55.5 | 65 | 69.5 | | |
| 6 | 63.5 | 36 | 76 | 66 | 45 | | |
| 7 | 63.5 | 37 | 49 | 67 | 53.5 | | |
| 8 | 70 | 38 | 55.5 | 68 | 70 | | |
| 9 | 69 | 39 | 58.5 | 69 | 47.5 | | |
| 10 | 52.5 | 40 | 46.5 | 70 | 73.5 | | |
| 11 | 73 | 41 | 82 | 71 | 64.5 | | |
| 12 | 75.5 | 42 | 68.5 | 72 | 72 | | |
| 13 | 69.5 | 43 | 86.5 | 73 | 66.5 | | |
| 14 | 70.5 | 44 | 53.5 | 74 | 56.5 | | |
| 15 | 59.5 | 45 | 41.5 | 75 | 68 | | |
| 16 | 71 | 46 | 68.5 | 76 | 71.5 | | |
| 17 | 42.5 | 47 | 77 | 77 | 71.5 | | |
| 18 | 74.5 | 48 | 69 | 78 | 69.5 | | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 19 | 47 | 49 | 84.5 | 79 | 78.5 | | |
| 20 | 49 | 50 | 71.5 | 80 | 75 | | |
| 21 | 68.5 | 51 | 53 | 81 | 58 | | |
| 22 | 62.5 | 52 | 71 | 82 | 71.5 | | |
| 23 | 57 | 53 | 87.5 | 83 | 67 | | |
| 24 | 60 | 54 | 81.5 | 84 | 60.5 | | |
| 25 | 69.5 | 55 | 93.5 | 85 | 61 | | |
| 26 | 71 | 56 | 84 | 86 | 70.5 | | |
| 27 | 51 | 57 | 82.5 | 87 | 57 | | |
| 28 | 63 | 58 | 67 | 88 | 40.5 | | |
| 29 | 71 | 59 | 53.5 | 89 | 57 | | |
| 30 | 55.5 | 60 | 45 | 90 | 53 | | |

# አባሪ መ-3

## የሴት ተማሪዎች የግንዛቤ መለያ ሙከራ ውጤት

| ተ. ቁ | የተገኘው ውጤት ከ100%ና የሙከራው አይነት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የግንዛቤ መለያ ሙከራ | | | | | | |
| | ከ100% | ተ.ቁ | 100% | ተ.ቁ | ከ100% | ተ.ቁ | ከ100% |
| 1 | 51 | 31 | 50 | 61 | 54 | 91 | 74 |
| 2 | 53 | 32 | 44 | 62 | 51 | 92 | 49 |
| 3 | 59 | 33 | 66 | 63 | 52 | 93 | 52 |
| 4 | 56 | 34 | 45 | 64 | 48 | 94 | 57 |
| 5 | 55 | 35 | 55 | 65 | 59 | 95 | 38 |
| 6 | 48 | 36 | 79 | 66 | 48 | 96 | 69 |
| 7 | 50 | 37 | 42 | 67 | 34 | 97 | 67 |
| 8 | 48 | 38 | 37 | 68 | 40 | 98 | 61 |
| 9 | 51 | 39 | 50 | 69 | 53 | 99 | 56 |
| 10 | 47 | 40 | 49 | 70 | 52 | 100 | 49 |
| 11 | 62 | 41 | 61 | 71 | 48 | 101 | 69 |
| 12 | 51 | 42 | 61 | 72 | 52 | 102 | 77 |
| 13 | 49 | 43 | 51 | 73 | 82 | 103 | 79 |
| 14 | 50 | 44 | 53 | 74 | 51 | 104 | 38 |
| 15 | 67 | 45 | 60 | 75 | 63 | 105 | 60 |
| 16 | 71 | 46 | 63 | 76 | 50 | | |
| 17 | 50 | 47 | 55 | 77 | 52 | | |
| 18 | 48 | 48 | 47 | 78 | 50 | | |
| 19 | 71 | 49 | 39 | 79 | 52 | | |
| 20 | 60 | 50 | 52 | 80 | 54 | | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 21 | 46 | 51 | 75 | 81 | 46 | | |
| 22 | 46 | 52 | 44 | 82 | 66 | | |
| 23 | 60 | 53 | 49 | 83 | 55 | | |
| 24 | 74 | 54 | 76 | 84 | 57 | | |
| 25 | 57 | 55 | 35 | 85 | 52 | | |
| 26 | 50 | 56 | 56 | 86 | 65 | | |
| 27 | 75 | 57 | 43 | 87 | 52 | | |
| 28 | 52 | 58 | 47 | 88 | 49 | | |
| 29 | 37 | 59 | 35 | 89 | 52 | | |
| 30 | 64 | 60 | 51 | 90 | 63 | | |

# አባሪ መ-4

## የሴት ተማሪዎች የቃል ጽህፈት ሙከራ ውጤት

| ተ.ቁ | የተገኘው ውጤት ከ100%ና የሙከራው አይነት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የቃል ጽህፈት ሙከራ | | | | | | |
| | ከ100% | ተ.ቁ | 100% | ተ.ቁ | ከ100% | ተ.ቁ | ከ100% |
| 1 | 72.5 | 31 | 77.5 | 61 | 83.5 | 91 | 75 |
| 2 | 71 | 32 | 49.5 | 62 | 67 | 92 | 79 |
| 3 | 70.5 | 33 | 74.5 | 63 | 78.5 | 93 | 73.5 |
| 4 | 74 | 34 | 59 | 64 | 66 | 94 | 55.5 |
| 5 | 68 | 35 | 79.5 | 65 | 78 | 95 | 49.5 |
| 6 | 62.5 | 36 | 70 | 66 | 70.5 | 96 | 87 |
| 7 | 52.5 | 37 | 43.5 | 67 | 38 | 97 | 68 |
| 8 | 63.5 | 38 | 79 | 68 | 46.5 | 98 | 63.5 |
| 9 | 62 | 39 | 77.5 | 69 | 75.5 | 99 | 77.5 |
| 10 | 70 | 40 | 42 | 70 | 58 | 100 | 47 |
| 11 | 69.5 | 41 | 35 | 71 | 76 | 101 | 58.5 |
| 12 | 66.5 | 42 | 82 | 72 | 74 | 102 | 59 |
| 13 | 66 | 43 | 78.5 | 73 | 81 | 103 | 83.5 |
| 14 | 74 | 44 | 74 | 74 | 78.5 | 104 | 51.5 |
| 15 | 62.5 | 45 | 78.5 | 75 | 74.5 | 105 | 83.5 |
| 16 | 89.5 | 46 | 65 | 76 | 87 | | |
| 17 | 76.5 | 47 | 52 | 77 | 50.5 | | |
| 18 | 65 | 48 | 75 | 78 | 62 | | |
| 19 | 80 | 49 | 82 | 79 | 70 | | |
| 20 | 59 | 50 | 83.5 | 80 | 69.5 | | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 21 | 69 | 51 | 57 | 81 | 84 | | |
| 22 | 67 | 52 | 68.5 | 82 | 74 | | |
| 23 | 75 | 53 | 51 | 83 | 69.5 | | |
| 24 | 79.5 | 54 | 64 | 84 | 74.5 | | |
| 25 | 79 | 55 | 72.5 | 85 | 79 | | |
| 26 | 48.5 | 56 | 78 | 86 | 77.5 | | |
| 27 | 50 | 57 | 59 | 87 | 54 | | |
| 28 | 53 | 58 | 81 | 88 | 46.5 | | |
| 29 | 48.5 | 59 | 54.5 | 89 | 72 | | |
| 30 | 50.5 | 60 | 78 | 90 | 78 | | |

## አባሪ - ሠ 1

**የግንዛቤ መለያ ሙከራዎች ትክክለኛነት በ KR- 21 ቀመር ተሰልቶ**

KR-21= [n/(n-1) x [1-(M x (n-M)/(n x $SD^2$))]

n= 100

M= 53.89

SD=10.43

R= (100/100-1) x [1-( 53.89 x (100-53.89)] / [100 x $10.43^2$)

R= 100/99 x [1- (53.89 x 46.11) / (100 x 108.78)

R= 100/99 x 1- 2484.87 / 10878

R= 1.0101 x 1 — 0.2284

R= 1.0101 x 0.7716

R= **0.78**

## አባሪ - ሠ 2

**የቃል ጽህፈት ሙከራዎች ትክክለኛነት በ KR- 21 ቀመር ተሰልቶ**

KR-21= [n/(n-1) x [1-(M x (n-M)/(n x $SD^2$))]

n= 100

M= 66.29

SD= 10.71

R= (100/100-1) x [1-( 66.29 x (100-66.29)] / [100 x $10.71^2$)

R= 100/99 x [1- (66.29 x 33.71) / (100 x 114.7041)

R= 100/99 x 1- 2234.6359 / 11470.41

R= 1.0101 x 1 — 0.1948

R= 1.0101 x 0.8052

R= **0.81**

# አባሪ - ረ

**የግንዛቤ መለያ ሙከራዎች የ ፎግ ኢንዴክስ ስሌት**

1. **የግንዛቤ መለያ ሙከራ 1**

- የቃላት መጠን- 309
- የአረፍተ ነገር ብዛት- 26
- የከባድ ቃላት ብዛት- 11
  - 309/26 = 11.89
  - 11.89 + 11 = 22.89
  - 22.89 x .4 = **9.156**

2. **የግንዛቤ መለያ ሙከራ 2**

- የቃላት መጠን- 347
- የአረፍተ ነገር ብዛት- 23
- የከባድ ቃላት ብዛት-9
  - 347/23 = 15.08
  - 15.08 + 9 = 24.08
  - 24.08 x .4 = **9.63**

# አባሪ - ሰ

**የቃል ጽህፈት ሙከራዎች የፎግ ኢንዴክስ ስሌት**

1. **የቃል ጽህፈት ሙከራ 1**
   - የቃል መጠን- 133
   - የአረፍተ ነገር መጠን-8
   - የከባድ ቃላት መጠን- 6
     - 133/10 = 16.6
     - 16.6 + 6 = 22.6
     - 22.6x 0.4 = **9.04**
2. **የቃል ጽህፈት ሙከራ 2**
   - የቃል መጠን- 124
   - የአረፍተ ነገር መጠን- 10
   - የከባድ ቃላት መጠን- 12
     - 124/10 = 12.4
     - 12.4 + 12 = 24.4
     - 24.4 x 0.4 = **9.76**